
# ትንሣኤ



አዲስ አበባ ከተማ በስተደቡብ በመታነፅ ላይ የሚገኘው ቡልቡላ ፈለገ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ፡

ቁጥር ፹፱ ሐምሌ ፲፱፻፸፮ ዓ.ም.



ብፁዕ አቡነ ናትናኤል የአርሲ ሀ/ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ከሰበካ ጉባኤ ተወካዮችና የጀኛ ሰበካ መ/ ጉባኤ ሥምሪት ልዑካን ጋር ፡

ዋጋው ኦ፩ ብር

www.ethiopianorthodox.org

«ይህ መጽሔት የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ታሪክ ፤ ሥርዓትና ዜና ፤ ልማትና የግብረ ገብነት ትምህርት በተግባር ጭምር እንዲተረጕሙ ለሥራ እንነሣ የሚል ስለሆነ "ትንሣኤ" ተብሎ ተሰይሟል ።»


አዘጋጅ
ልሣነወርቅ በዛብኅ ፤
ም በለጠ አበበ


በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልዕኮ መምሪያ የሥነ ጽሑፍ ክፍል ተዘጋጅቶ በወር አንድ ጊዜ እየታተመ የሚወጣ ።

የስልክ ቁጥር 110754
የመልእክት ሣ. ቁ. 3137
አዲስ አበባ ፤


## ማ ው ጫ

**አርእስት ፤** **ገጽ**


ደብዳቤዎች ............ ፩
የቤተ ክርስቲያናችን መሠረት ብሉይና ሐዲስ ናቸው ............ ፪
አንድነት በሦስትነት ............ ፬
ልማት በቤተ ክርስቲያን ............ ፮
መሠረተ ሕይወት (የሕይወት መጀመሪያ) ............ ፰
ዜና ሊቃውንት ............ ፲
ጾመ ፍልሰታ ............ ፲፩
የጽድቅ ፍሬ ............ ፲፪
ክበለስ በታች አየውህ ............ ፲፫
የአባ ኃይለ መለ ኮት አጭር የሕይወት ታሪክ ............ ፲፬
የሐውልት ምረቃ ............ ፲፯
የግብርና በረከት ............ ፲፰
ሕፃኑ ከእናቱ ጋር ............ ፳
ማንን ላግባ ? ............ ፳፩


ለትንሣኤ መጽሔት አዘጋጅ
አዲስ አበባ

አንድ በጣም የቸገረኝ ነገር አለ ጉዳዩም የሚከተለው ነው በሻሸመኔ ወረዳ ልዩ ስሙ ሶሎ መድኀኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን አካባቢ በተግባር ያልታወቁ በስም ብቻ ቄስ ነኝ የሚሉ አንድ ሰው አሉ ሰውየው ቄስ መሆናቸውን ይናገራሉ እንጂ የቅስና ትምህርት ምንም ያልተማሩ መሆናቸው በአሠራራቸውና በአገልግሎታቸው ይታወቃሉ ።

ለመሆኑ ሥልጣነ ክህነት በሚሰጥበት ጊዜ ፈተና የለም ወይ? ፈተና ካለስ ፈተናውን አልፈው የቅስናን ሥልጣን እንዴት ሊቀበሉ ቻሉ ?

፪ኛ/ ጋብቻ በተክሊል መፈጸም አለበት ይባላል ፤ ጋብቻ በተክሊል መፈጸም የተጀመረው መቼ ነው ?

፫ኛ/ ቄስ ከሚስቱ ጋር ስምምነት አጥቶ ቢፋታ ወይም ሚስቱ ብትሞትበት ልጃገረድ አግብቶ አይቀድስም ወይ?

፬ኛ/ ለታቦት መስገድ የተጀመረው ከመቼ ወዲህ ነው ?

ለእነዚህ አራት ጥያቄዎች መልስ እንድትሰጡኝ በተስፋ እጠባበቃለሁ ።

መምሬ አካሉ አየለ
ሻሸመኔ ከተማ ሶሎ መድኀኔ ዓለም አካባቢ

መልስ ፤

መምሬ አካሉ አየለ ስለአቀረቡአቸው ጥያቄዎች እናመሰግናለን ።

ከመጀመሪያው ጥያቄዎ ላይ ሥልጣነ ክህነት ሲሰጥ ፈተና የለም ወይ ? ስላሉት ያለፈተና ሥልጣነ ክህነት አይሰጥም አስፈላጊው ፈተና ከተሰጠ በኋላ ሥልጣን የሚቀበለው ቤተ ክርስቲያንን ለማገልገል ብቁ ሆኖ የተገኘ እንደሆነ ይሰጠዋል ብቁ ሆኖ ካልተገኘ ደግሞ ያላሟላውን የትምህርት ዓይነት ተምሮ አሟልቶ እንዲመጣ ምክር ተሰጥቶት ይሄድና የተባለውን አሟልቶ ሲመለስ ሥልጣነ ክህነት ይሰጠዋል እንጂ እንዲሁ ሳይፈተን ቄስም ሆነ ዲያቆን ሥልጣን አይሰጠውም

፪ኛ/ ጋብቻ በተክሊል መፈጸም የተጀመረው በገሊላ አውራጃ ቃና በምትባል ቀበሌ ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከእናቱ ቅድስት ድንግል ማርያምና ከደቀ መዛሙርቱ ጋር በተገኘበት ሲሆን ይኸውም በመጀመሪያው መቶ ዓመት መሆኑ ነው ዮሐ ፪

፫ኛ/ ቄስ ሚስቱ ብትሞትበትም ከሚስቱም ጋር ስምምነት በማጣት ቢለያይም ልጃገረድ አግብቶ እንዲቀድስ ሕገ ቤተ ክርስቲያን አይፈቅድለትም ።

፬ኛ/ ለታቦት መስገድ የተጀመረው በሙሴ ጊዜ ነው ዘፀ. ፴፬.፰ ላይ ቢመለከቱ በሰፊው ለመረዳት ይችላሉ ።

ለትንሣኤ መጽሔት አዘጋጅ
አዲስ አበባ

በመጀመሪያ በጌታችን በመድኀኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም የከበረ መንፈሳዊ ሰላምታ አቀርባለሁ ከሰላምታዬ ቀጥዬ የሚከተለውን ጥያቄ አቀርባለሁ ።

እመቤታችን ድንግል ማርያም በዚህ ዓለም ፷፬ ዓመት ኑራ ባረፈች ጊዜ ሐዋርያት ተሰብስበው በአልጋ ላይ አድርገው ሊቀብሩ ወደጌቴሴማኒ ይዘዋት ሲጓዙ አይሁድ በምቀኝነት ተነሣሥተው የድንግል ማርያምን ሥጋ ለማቃጠል ወደአስከሬኑ ቀረቡ፤ከእነርሱም መካከል ታውፋንያ የተባለ አይሁዳዊ የአልጋውን ሸንኮር በያዘው ጊዜ መልአኩ በሰይፍ ሁለት እጆቹን ቀረጠው ወዲያው አይሁዳዊው በእግዚአብሔር አምኖ በድንግል ማርያም ተማፀነ ድንግል ማርያምም ሐዋርያው ጴጥሮስ ጸልዩ እጆቹ ተመልሰው እንዲቀጠሉ አስደረገችለት ።

ሐዋርያት ግን አይሁድን ስለፈሩ ተበታተኑ የእመቤታችን ሥጋ ከዮሐንስ ጋር በደመና ነጥቆ ወስዶ በገነት ከዕፀ ሕይወት ሥር አስቀመጣት የሚል ተአምር ተጽፏል በሌላ በኩል ደግሞ ሐዋርያት መንፈስ ቅዱስን ከተቀበሉ በኋላ የፍርሃት መንፈስ ፈጽሞ ተወግዶላቸው ደፋሮች ስለሆኑ አልሸሹም የሚል ተአምር ሲነበብ ሰምቻለሁ ።

እንግዲህ አንደኛው ተአምር ሸሽተዋል ሌላው ደግሞ አልሸሹም ካለ ለእኛ ለአድማጮች ግራ የሚያጋባ ስለሆነ በትንሣኤ መጽሔት ይህንን በደንብ አብራርታችሁ እንድትገልጹልኝ መልሱን በተስፋ እጠባበቃለሁ ።

ዕሜቴ ለማ መተሐራ ደብረ ሰላም
መድኀኔ ዓለም

ወ/ት ዕሜቴ ለማ ስላቀረብሽልን ሰላምታ እያመሰገን ለጥያቄው መልስ እንሰጣለን ተአምሩ አንቺ እንደሰማሽው ተጽፎ መገኘቱ ዕርግጥ ነው ሐዋርያው ጳውሎስ "እስመ ንባብ ይቀትል ወትርጓሜ የሐዩ" ንባብ ይገድላል ትርጓሜ ግን ያድናል ። ይላል የሚነበበው መጽሐፍ ሁሉ መተርጕማን ያስፈልጉታል መተርጕማን መጻሕፍት መምህራን ከሌሉ ጥርጥር ክህደት በትንሽ ምክንያት ሊፈጠር ይችላል ስለዚህ አባቶች መምህራን ባይኖሩ መጻሕፍት እርስ በእርሳቸው በተበላሉ ነበር ይላሉ ።

ሐዋርያት አይሁድ በመጡባቸው ጊዜ ፈርተው ተበታተኑ ማለቱ ክርስቶስ የድንግል ማርያምን ሥጋና ዮሐንስን በደመና ነጥቆ ሲወስዳቸው ሐዋርያት ወደ የሀገረ ስብከታቸው ተመልሰው የስብከተ ወንጌል ሥራቸውን ቀጠሉ ማ

ወደ ፰ኛው ገጽ ዞሯል



www.ethiopianorthodox.org

ርእሰ አንቀጽ

# የቤተ ክርስቲያናችን መሠረት ብሉይና ሐዲስ ናቸው

ባለፈው ኅንቦት ከ፲፩ እስከ ፲፰ ቀን ቀን ፲፱፻፸፯ ዓ.ም. ሁለተኛ አጠቃላይ መንፈሳዊ ጉባኤ በአዲስ አበባ ከተማ በመንበረ ፓትርያርክ ስብከተ ወንጌል አዳራሽ መደረጉ የሚታወስ ነው ።

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ይህንን ታላቅ ጉባኤ በጸሎተ ቡራኬ በከፈቱበትና በሊቀ መንበርነት በመሩበት ጊዜ ባደረጉት ንግግር የቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ሥር መሠረቷ ብሉይና ሐዲስ ናቸው ። በአሁኑ ጊዜ የብሉይና የሐዲስ ጉባኤ የሚነገሩት በጥቂቶች ቦታዎች ነው ።

ወደፊት ነበሩ ቀሩ እንዳይባሉ የጉባኤ መምህራን በሚያስፈልጉበት ቦታ እየተመደቡ ማስተማር አለባቸው ይህ የሆነ እንደሆነ ቤተ ክርስቲያናችን በሃይማኖት ጸንታ በመልካም ምግባር በልጽጋ ለመኖር ትችላለች ። ስለዚህ የብሉይና የሐዲስ ጉባዔ የሚያስተምሩ መምህራን በሰበካ ጉባዔ ገቢ እየተቀጠሩ እንዲያስተምሩ ያስፈልጋል ካሉ በኋላ ቅዱስነታቸው ንግግራቸውን በመቀጠል ለማንኛውም ሥራ ተተኪ ያስፈልገዋል ። ፡ ቀድሞ የነበሩት መምህራን ሲያረጁና በሞት ከዚህ ዓለም ሲለዩ በእነርሱ እግር ተተክተው የሚያስተምሩ የጉባኤ መምህራን ከሌሉ ለቤተ ክርስቲያናችን ታላቅ ችግር ይሆናል ።

በሊቃውንቱ ሲነገርና ሲገለጽ የኖረው የቤተ ክርስቲያናችን ምሥጢር የተሠወረ ሆኖ እንዳይቀር የማስተማር ችሎታ ያላቸው የጉባኤ መምህራን በብዛት ተቀጥረው እንዲያስተምሩ ካሉ በኋላ መምህራን ካላስተማሩና ተማሮችም ካልተማሩ በቤተ ክርስቲያናችን ላይ ከፍ ያለ ጉዳት ሊደርስ ይችላል ጉዳቱ ግን የሚታወቀው አሁን ሳይሆን በሚቀጥለው ትውልድ ነው ሲሉ ተናግረዋል ቅዱስነታቸው ንግግራቸውን በማራዘም የምንሠራው ሥራ ሁሉ መሠረት ያለው ሊሆን ይገባል ።ሥራችን ከላይ ከላይ የሆነ እንደሆነ መሠረት አይኖረውም ሃይማኖታችን የሚጸናውና ሥራችንም ሥር መሠረት ሊኖረው የሚችለው ከላይ እንደጠቀስኩት የብሉይና የሐዲስ ጉባኤ መምህራን በብዛት ተቀጥረው በማስተማር ትምህርቱ ሲስፋፋ ነው ። አሁንም ደግሜ የማሳስበው የብሉይና የሐዲስ ጉባዔ ለሚያስተምሩ መምህራንና ለሚማሩ ደቀ መዛሙርት እንክብካቤ እንዲደረግላቸው ነው በማለት ቅዱስነታቸው ንግግራቸውን አጠቃለዋል ።

ጉባኤውም የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖትን ቃል መነሻ በማድረግ ሰፋ ያለ ውይይት አድርጎ በመጨረሻ በየአህጉረ ስብከቱ የሚገኙ ሊቃነ ጳጳሳት በሚገባ አስበውበት ጉዳዩ አስፈላጊ ስለሆነ በሥራ እንዲተረጐም ውሳኔ አስተላልፏል ።

"እስመ ብዝኃ ጠበብት መድኃኒተ ዓለም ውእቱ" የመምህራን ብዛት የዓለም መድኃኒት ነው" ብሎ ጠቢቡ ሰሎሞን እንደተናገረው ለቤተ ክርስቲያናችን አሁን ከሚገኙት የሚበዙ የጉባኤ መምህራን ያስፈልጋታል የብሉይና የሐዲስ ጉባኤ መምህራን ሲበረከቱ ሃይማኖት ይጸናል ፣ በጎ ምግባር ይስፋፋል ።

በሀገራችን ከሃያ ሺ በላይ የሚሆኑ አብያተ ክርስቲያናት ከሁለት መቶ ሺ የማያንሱ ካህናት መኖራቸው ተደጋግሞ በጽሑፍም በቃልም ይነገራል ከተጠቀሱት ካህናት መካከል የማስተማር ችሎታ ያላቸው መምህራን ግን በቁጥር አነስተኞች ናቸው ።

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት በንግግራቸው ላይ እንደገለጹት ቀደም ሲል የነበሩት መምህራን በሞት ከዚህ ዓለም ሲለዩ በእነርሱ ቦታ ተተክተው የሚያስተምሩ መምህራን በመታጣቸው አንዳንድ ታላላቅ አድባራትና ገዳማት ያለ መምህራን መታየታቸው አልቀረም ።

ዓለም ወደፊት በሥልጣኔ ይገሠግሣል እንጂ ወደ ኋላ ተመልሶ የድንቁርና ድንጊያን በራሱ ላይ ተሸክሞ ለመንገዳገድ አይሻም ። እርቃነ ሥጋውንም ቆሞ ለመታየት አይፈልግም አሁን ሰው የሆነ ሁሉ ከልብስ ልብስን እያማረጠ በመልበስ ከሚያጌጥበት ደረጃ ላይ ደርሷልና በሥራም በኑሮም በምግብም በኩል የቀድሞውና የአሁኑ እጅግ በጣም የተራራቀ ነው ።

በሠለጠኑት ሀገሮች ከአራትና ከአምስት ዓመታት በፊት ይጠቀሙበት የነበረውን የሥራ ይዞታ አሁን አይጠቀሙበትም ሥራቸውንና መሣሪያቸውን በየጊዜው እያሻሻሉ በመሥራት ለቤተ ክርስቲያናቸው ከፍ ያለ



መንፈሳዊ አገልግሎትን ያቀርባሉ ከዚህም የተነሣ ራሳቸውን ችለው ሌላውንም ከሚረዱበት ደረጃ ላይ ደርሰው ይገኛሉ ።

ወደ እኛ ቤተ ክርስቲያን ዓይነ ልቡናችን መልስ አድርገን ስንመለከት ደግሞ ብዙ ሊሻሻሉ የሚገባቸው ነገሮችን እናገኛለን ። ሊሻሻል የማይችል ሃይማኖት ነው እንጂ የቀረውን የአሠራር ዘዴ እንደአስፈላጊነቱ ወቅቱን ጠብቆ ጊዜውን ተከትሎ ቢሠሩት ያስመሰግናል እንጂ አያስነቅፍም ።

ለምሳሌ በበሬ ጉልበት እያረሰ ራሱ በዶማ እየቆፈረ አነስተኛ ምርት ያመርት የነበረው ገበሬ አሁን በሰለጠነው ዓለም ሥልጣኔ በወለደው መሣሪያ በትራክተር በማረስ ብዙ ምርትን ቢያመርት ይመሰገናል እንጂ አይነቀፍም እንደዚሁም የቀደሙ አባቶችም ሲያስተምሩና ሲማሩ የሚረዳቸው አልነበረም ፣ አንዳንዶች መምህራን ተማሮች ስመ እግዚአብሔር በመጥራት ለምነው ያመጡትን ቁራሽ እንጀራ ከተማሮቻቸው ጋር እየተመገቡ ሲያስተምሩ ሌሎች ደግሞ በደብሩ ሰበካ የሚኖረው ሕዝብ በሚያደርግላቸው አስተዋጽኦ በመረዳት ያስተምሩ ነበር ። ተማሮችም አኩፋዳቸውን ይዘው ቁራሽ እንጀራ ከሕዝቡ እየለመኑ በመመገብ ከመምህራኑ ትምህርት በነፃ ሲሰጣቸው ኑረዋል ።

በዚህ ዓይነት ቤተ ክርስቲያናችን እምነቷን አጽንታ ሥርዓቷን ጠብቃ ኑራለች ። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ ቤተ ክርስቲያን የምትተዳደርበትን ቃለ ዓዋዲ አሻሽሎ በማውጣት መምህራን ተግተው እንዲያስተምሩ ተማሮችም እንዲማሩ አመች መንገዶችን በመቀየስ ላይ ይገኛል ።

ምን እንበላለን ምን እንለብሳለን የሚለው አሳብ ከመምህራንና ከተማሮች ተወግዶ ያለምንም ችግር እንዲያስተምሩና እንዲማሩ ካህናት ተባብረው ሰበካ ጉባኤን የማቋቋምና የማጠናከር ግዴታ አለባቸው ።

ከቅርብ ቀን ወዲህ በአንዳንድ አህጉረ ስብከት የብሉይና የሐዲስ ጉባኤ መምህራን እየተቀጠሩ በማስተማር ላይ መሆናቸው ታውቋል ከተማሮችም የዕለት ጉርስ የዓመት ልብስ እየተሰጣቸው ትምህርታቸውን የሚከታተሉ መኖራቸው አይካድም ቢሆንም አሁን ያሉት የብሉይና የሐዲስ ጉባኤ መምህራን በቂ ስለማይሆኑ ቁጥራቸው በርከት ብሎ ለመምህራኑም ሆነ ለተማሮቹ አስፈላጊው እንክብካቤ እንዲደረግላቸው ሲሉ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት የሰጡት አባታዊ መመሪያ እውን እንዲሆን በየአህጉረ ስብከቱ የሚገኙ ሊቃነ ጳጳሳት የመተባበር ግዴታ አለባቸው እንላለን ።



www.ethiopianorthodox.org

# አንድነት በሦስትነት ፡

በቀዳሚ ገብረ እግዚአብሔር ሰማየ ወምድረ ማለት እግዚአብሔር በመጀ መሪያ ሰማይና ምድርን ፈጠረ ዘፍ ፩፣ ቁ. ፩
የእግዚአብሔርም መንፈስ በውሃ ላይ ነበር

እግዚአብሔርም ብርሃን ይሁን አለ
እግዚአብሔር ብርሃንና ጨለማን ለየ

እግዚአብሔርም ብርሃኑን ቀን ብሎ ጠራው ጨለማውንም ሌሊት አለው ። እግዚአብሔርም በውኃዎች መካከል ጠ ፈር ይሁን አለ ፡ እግዚአብሔር ጠፈርን ሰማይ ብሎ ጠራው ።

እግዚአብሔርም ከሰማይ በታች ያለ ውን ውሃ በአንድ ስፍራ ይሰበሰብ የብ ሱም ይገለጥ አለ ። እግዚአብሔር ያ መልካም እንደሆነ አየ ።
እግዚአብሔር ምድር ዘርን የሚሰጥ ሣ ርንና ቡቃያን እንደወገኑ ዘሩም ያለበት ፍሬን የሚያፈራ ዛፍ ታብቅል አለ ።
እግዚአብሔር ቀንና ሌሊትን ይለዩ ዘንድ ብርሃናት በሰማይ ጠፈር ይሁኑ ለምልክቶች ለዘመኖች ለዕለታት ለዓ. መታትም ይሁኑ አለ ።
እግዚአብሔርም ሁለት ታላላቆች ብር ሃናትን አደረገ ።
ትልቁ ብርሃን በቀን እንዲሰለጥን ትን ሹም ብርሃን በሌሊት እንዲሰለጥን አደረገ ።
እግዚአብሔርም በምድር ላይ ያበሩ ዘን ድ በሰማይ ጠፈር አኖራቸው ።
በአራተኛው ቀን እግዚአብሔርም አለ ው-ን ነፍስ ያላቸውን ተንቀሳቃሾች ታ ስገኝ ወፎችም ከምድር በላይ ከሰማይ ጠፈር በታች ይብረሩ ።
እግዚአብሔርም እንዲህ ብሎ ባረካቸው ብዙ ተባዙም ምድርንም ሙሉአት ። ተን ቀሳቃሾችን እንደ ወገኑ አደረገ እግዚአ ብሔርም ያ መልካም እንደሆነ አየ ።
በስድስተኛው ቀን እግዚአብሔርም ሰውን በመልካችን እንደምሳሌያችን እንፍጠር አለ ።
የተፈጠሩትን ፍጥረታት ይገዙ ዘንድ እግዚአብሔርም ሰውን በመልኩ ፈጠ ረ በእግዚአብሔር መልክ ፈጠረው ወን



ሥላሴ በአካል ሦስት በመለኮት አንድ ናቸው



ድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው ዘፍ፣ ከም. ፩ቁ.፩-፳፱ያሉትን ነጥቦችእንመልከት፣ እግዚአብሔር እንዲህ ያሉትን ፍጥረ ታት ፈጠረ እያለ መጥቶ ከቁጥር 26 ሲደርስ የሰውን ተፈጥሮ በተናገረበት ቁጥር የእግዚአብሔርን አንድነትና ሦ ስትነት ሲያስረዳ ሰውን በምሳሌያችን እንፍጠር በማለት ምሥጢረ ሥላሴን እሱ ባለቤቱ አስተማረን ሌላ አስተማሪ የለንም መጀመሪያ አስተማሪያችን እግ ዚአብሔር አምላክ ነው ። በሁለተኛም ደረጃ ወይቤ እግዚአብሔር አዳም ኮነ ከመ አሐዱ እምኔነ አዳም ከኛ እንዳንዱ ሆነ አለ እግዚአብሔር እያለ ባለቤቱን አንቀጹን ያንድ በሳቡን ዝርዝሩን በብ ዙ እያደረገ እግዚአብሔር አንድ ሲሆን ሦስት ሦስት ሲሆን አንድ መሆኑን መጽ ሐፍ ቅዱስ ያስረዳናል ።

እንዲሁም ዘፍ ፲፩ ቁጥር ፯ አንዱ ያንዱን ነገር እንዳይሰማ ኑ እንውረድ ቋንቋቸው ንም እንደባልቅባቸው አለ እግዚአብሔር ብሎ ምስክር ይገኛል ። በአብርሃም ዘመን በአጸደ መምሬ ለአብ ርሃም የተገለጡት ሦስቱ አካላት ነበሩ የነሱንም ስም ገልጦ ያስተማረን ከሦ ስቱ አካላት አንድ አካል ሰውን ለማ ዳን ሰው የሆነው መድኃኒታችን ኢየ ሲስ ክርስቶስ ነው ።
ሱስ ክርስቶስ ነው ።
ነት ወደ ዓለም ሲልካቸው ሄዱና እስከ ዓለም ዳርቻ ድረስ ወንጌልን አስተምሩ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም አጥምቋቸው ብሎ ግልጥ አድርጎ እስከ ሚያስተምራቸው ድረስ ምንም አካላት በሦስትነት ገጽ ቢገለጡና ቢታዩ እንኳ አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ማለት አል ታወቀም አልተገለጠም ነበር ።

ስለዚህ ቤተ ክርስቲያንን የመሠረ ታት ክርስቶስ ተቀባዮቹ አባቶች ሐዋ ርያት ቀጥለው የተነሱ ሊቃውንት ስለአ ንድነትና ሦስትነት ያስተማሩትንና የሰ ጡትን መመሪያ አርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያናችን ታምናለች ታሳም ናለች ስለቅድስት ሥላሴ የሰጡትን ት ምህርት ታስተምራለች ።

ቅድስት ሥላሴ አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ይባላሉ (የአብ ግብሩ መወለድ የወልድ ግብሩ መወለድ ፣ የመንፈስ ቅዱስ ግብሩ መሰረጽ ነው ። አብ ቢወ ልድ ቢያሠርጽ እንጂ እንደ ወልድ አይወለድም እንደ መንፈስ ቅዱስ አይ ሠርጽም ወልድም ቢወለድ እንጂ እንደ አብ አይወልድም አያሠርጽም እንደ መንፈስ ቅዱስ አይሠረጽም መንፈስ ቅዱስ ቢሠርጽ እንጂ እንደአብ አይወ ልድም አያሠርጽም እንደ ወልድ አይ ወለድም ለአብ ፍጹም አካል ገጽ ፍጹም መልክ አለው ለወልድም ፍጹም አካል ገጽ ፍጹም መልክ አለው ። ለመንፈስ ቅዱስ ስም ፍጹም አካል ፍጹም ገጽ መ ልክ አለው ።

እነዚህም ኩነታት ይባላሉ ኩነታት በተከፍሎ በተፈልጦ ያለመጠቅለል ያለመቀላቀል በየራሳቸው ጸንተው በአ ንድ መለኮት የነበሩ ያሉ የሚኖሩ ናቸ ው ። እነሱም ልብነት ቃልነት እስትን ፋስነት ናቸው ልብነት በአብ መሠረት ነት ለባዊ ሆኖ ለወልድ ለመንፈስ ቅዱ ስ ልብ ዕውቀት መሆኑ ነው ።

ቃልነት በአብ መሠረትነት ለራሱ ለባቢ ቃል ሁኖ ለአብ ለመንፈስ ቅዱስ ንባብ ቃል መሆን ነው ። እስትንፋስ ነት በአብ መሠረትነት ለራሱ ሕያው ሁኖ ለአብ ለወልድ ሕይወት መሆን ነው ።

ስለዚህ በአብ ልብነት ወልድ መን ፈስ ቅዱስ ህልዋን ናቸው ያስቡበታል በወልድ ቃልነት አብ መንፈስ ቅዱስ ህልዋን ናቸው ይናገሩበታል ። በመን ፈስ ቅዱስ እስትንፋስነት አብ ወልድ ህልዋን ናቸው ሕያዋን ሁነው ይኖሩበ ታል ። ዮሐ. ፲፬/ቁ/፲/፲፪ ቁ. ፵፱ ም ፩ - ፴፰ በስም በግብር በአካል ሦስት ቢባሉ አንድ አምላክ ይባላል እንጂ ሦ ስት አማልክት አይባሉም ።

ሥላሴ በዘመን አይቀዳደሙም በክ ብር አይበላለጡም ሥላሴን በዘመን በክ ብር አበላልጦ ቢገኝ ከእነአርዮስ ከነን ስጥሮስ ከነመቅዶንዮስ ቤተ ክርስቲያ ናችን ለይታ አታየውም እነሱ እንደተ ወገዙና እንደተለዩ አውግዛ ትለያቸዋ ለች ።

ስለዚህ ከአዕማድ ቀዳሚውና መጀ መሪያው እግዚአብሔር በአካላት በኩነ ታት ሦስት በባሕርይ በህልውና በሥል ጣን በምልዓት በመለኮት አንድ አም ላክ ብለን እናምናለን እናስተምራለን ።
ሊቀ ኅሩያን መርሐ ጽድቅ ገ ሕይወት

---

# ደብዳቤዎች

ከገጽ ፩ የዞረ

ለት ነው እንጂ ፈርተው ተበታተኑ ማ ለት እንዳልሆነ ሁላችንም ማወቅ ይኖር ብናል ሐዋርያት ይፈሩ የነበሩ ገና መን ፈስ ቅዱስ ሳይወርድላቸው ጥቡዓን ሳ ይሆኑ ነበር ።

መንፈስ ቅዱስ ከወረደላቸው በኋላ ፍርሃት ፣ ድንጋጤ ተወግዶላቸው በአረ ማውያን አደባባይ ቆመው ሳይፈሩና ሳያፍሩ በመመስከር የወንጌልን ቃል በዓለም ለማዳረስ ችለዋል ።

ወ/ት ዕሤቱ እንደጠየቅሽው ከሁ ለት ላይ ቃሉ ተጽፎ በመገኘቱ የት ኛው ነው ትክክል የሚለውን አስተሳ ሰብ መፍጠሩ አያጠራጥርም ለዚህ ትክ ክለኛው መልስ ሐዋርያት መንፈስ ቅዱ ስ ስላደረባቸው አልሸሹም የሚለው ነው ጥር ሃያ አንድ ቀን የሚነበበውም ስንክሣር ሐዋርያት አይሁድን ፈርተው ሸሹ አይልም እኛም እንዳንድ ሊቃውን ትን እነጋግረን የሰጡን መልስ ።

ምንአልባት ግድፈተ ጸሐፊ ይሆና ል እንጂ ሐዋርያት አይሁድን በመፍ ራት የእመቤታችን አስከሬን ትተው ሸሹ የሚል ቃል መጻፍ ተገቢ አይመስ ልም መንፈስ ቅዱስ ደፋሮች አድርጓቸ ዋልና በማለት አስተያየታቸውን ነግረ ውናል ዜና ፍልሰታ የተባለውም አል ሸሹም ይላል ። ያም ሆነ ይህ መልሱ እንደስንክሣር ስለሚመስል ስንክሣሩን ብንከተል የተሻለ ይመስለናል ። ወ/ት ዕሤቱም ጥር ሃያ አንድ ቀን የሚነበበ ውን ስንክሣር ተመልከተሽ በእርሱ እንድትመሪ ቢሆን መልካም ነው ።



www.ethiopianorthodox.org

# ልማት በቤተ ክርስቲያን

ክብዑዕ አቡነ ገሪማ በምድረ ሱዳን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ሊቀ ጳጳስና የልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ መምሪያ ተ ጸሐፊ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን የልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ መምሪያ በቤተክርስቲያናችን እንዣር ልማትንና ተራድኦን በሚመለ ከት ያለው ዓላማና አቋም

እድገት ከሆነ እድገትም የልማት ውጤት መሆኑ አያጠራጥርም ።

ሰው የተፈጥሮ ችሎታውን በትምህርት አጐልምሶ ሀገርን መገንባት የሰውንም ሕይወት ማልማት ይችላል ።

የክርስትና ሃይማኖት የአማልክት አምላኬዎችን ሥጋዊ ጥበብ ደምስሶ የ ብሉይ ኪዳኑንም ሃይማኖታዊ ሥልጣን በትምህርትና በተአምራት አሻሽሎ ከ አራተኛው መቶ ዓመት መነሻ ድረስ የእግዚአብሔርና የቄሣር ገንዘብ ተለ ይቶ በመታወቁ የእግዚአብሔር የሆነው ሁሉ በዓላማው ጸንቶ ለቆመለት ዓላማ ለእግዚአብሔር መንግሥት በመሥራት በዚያ አስፈሪና አስከፊ ጊዜ ለቤተክርስቲያን እድገትና ልማት የተሠራው በመጠኑና በዓይነቱ የላቀ ዋጋ ያለው መሆኑን ከታሪኩ እንረዳለን ፤



በሁለተኛ አጠቃላይ መ/ጉባኤ ላይ የተሳተፉት ሊቃነ ጳጳሳትና የጉባኤው አባላት በከፊል

ልማት የሚለው ቃል በተለያዩ ግለሰቦች የተለያየ ትርጉም ያለው ሲሆን ግን በብዙ ሊቃውንት አስተሳሰብ ልማት የዕድገት ወይንም የለውጥ ሂደት መሆኑ በግልጽ ይነገራል ። ልማት ከግለሰብ አስተሳሰብ በላይ የሆነ የዕድገት ሥራ መሆኑም የታወቀ ነው ። ልማት ዲስ ሕይወትን የመሠረተ መሆኑን እናውቃለን ።

እምነቱን በምግባረ ሠናይ የማይገልጽ ሰው ነፍስ እንደተለየው በድን መሆኑን መጽሐፍ ቅዱስ ያስተምረናል ። (ያዕቆብ ፪ ፤ ፲፬-፳፮)

ከአንደኛው መቶ ዓመት ጀምሮ እስ ግን ከአራተኛው መቶ ዓመት ጀምሮ የእግዚአብሔርና የቄሣር ሰዎች በአንድ አንፃር ተሰባጥረውና ተመሳጥረው ስለተሠለፉ የእግዚአብሔርንና የቄሣርን ገንዘብ ለይቶ ማወቅ አዳጋች በመሆኑ የቤተክርስቲያን ልማትና ግንባታ እየተዳከመ መምጣቱን ከጊዜው ታሪክ መረዳት እንችላለን ።



ኢትዮጵያ በአፍሪካ ክፍለ ዓለም በሰሜን ምሥራቅ የምትገኝ በተፈጥሮ የታደለች ለም ሀገር ስትሆን በተፈጥሮ አቀማመጥም "ቀርነ አፍሪካ" እየተባለች ትጠራለች ።

ኢትዮጵያ በአውሮፓም ሆነ በሌሎቹ ስነ ጽሑፍ "ኢትዮጵያ" ወይንም "አቢሲንያ" በመባል የታወቀች ሀገር ስትሆን ግን እኛ ፤ ሀገራችን ኢትዮጵያ እኛም ኢትዮጵያውያን መሆናችንን ደህና አድርገን እናውቃለን ።

ኢትዮጵያ የሚለውን ስመ ተፀውኦ በመጽሐፍ ቅዱስ በብዙ ቦታ እናገኛዋለን ።



ብፁዕ አቡነ ገሪማ ስለቤተክርስቲያን ልማት ሪፖርት ሲያቀርቡ

የሙሴ መጽሐፍ የሁሉንም ነገር አጀማመር የሚነገረን ልዩ መጽሐፍ በመሆኑ በኦሪት ዘፍጥረት በምዕራፍ ፪፣፲፫ ላይ የሁለተኛው ወንዝ ስም ግዮን ነው እርሱም የኢትዮጵያን ምድር ሁሉ ይከባል " ይላል ።

የሰው ዘር ሥልጣኔ ፤ ልማትና እድገት የተገኘው (የተጀመረው) ከውሀ ዳርቻ መሆኑን ታሪክ ይነግረናል ። ኢትዮጵያም እንደሌሎቹ ሀገሮች ጥንታውያን ወንዞችና የባሕር ዳርቻዎች ጥቁር ዓባይን ፤ ቀይ ባሕርንና የመሳሰሉት ያሏት ናት ።

በኢትዮጵያ የአክሱም ከተማ እድገት ከሌሎቹ በጥበባቸውና በሥልጣኔያቸው ከታወቁት ጥንታውያን ሀገሮች ሥልጣኔ ጋር የሚወዳደር እንደነበር ታሪክ ይነግረናል ።

ከክርስትና በፊት በኢትዮጵያ ስለነበረው የእምነት አመጣጥና የአምልኮት አፈጻጸም ብዙ የተነገረና የተጻፈ ታሪክ ቢኖርም በብዙዎቹ የታሪክ አጻጻፍ ጐልቶ የሚታየው ኢትዮጵያ በሙሴ ሕግ ትመራ የነበረ መሆኑ ነው ።

የክርስትናው ትምህርት በተለያየ አቅጣጫና ምክንያት ወደ ኢትዮጵያ የገባው በአንደኛው መቶ ዓመት በሐዋርያት ዘመን ሲሆን የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ሕልውና ታውቆ ምሥጢራተ ቤተክርስቲያንን መፈጸም የተጀመረውም ከአራተኛው መቶ ዓመት እንሥቶ መሆኑ ግልጽ ነው ።

ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ባሏት የታሪክ ዘመናት ሁሉ ከመንፈሳዊው አገልግሎት ጋር የልማትን ሥራ በኅብረተሰቡ መካከል በማስፈን ኅብረተሰቡን በእኩልነት ደረጃ ስታገለግል የኖረች ሐዋርያዊት ቤተ ክርስቲያን ናት ።

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌለ መንግሥቱን በማይናወጥ ሕይወታዊ መሠረት ላይ አደላድሎ ከማረጉ በፊት ምድራውያን ሰዎችን አስተምሮ እንደነሱ ያሉ ተከታዮችን እንዲያዘጋጁ የሰጣቸው መመሪያ "ሑሩ ወመሐሩ" የሚለውን ነው። (ማቴ) ፳፰ ፤ ፲፱)

ሁሉም ሰው እንደ አእምሮው ስፋትና እንደ እውቀቱ መጠን በሀሳቡ የደረሰበትን በልቡ ያሰበውን በማናቸውም ጊዜና ቦታ የመሰለውን ነገር ሲያመልክ መኖሩን ከሃይማኖት ታሪክ እንረዳለን ።

የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ልማትና ዕድገት በተለያየ ጊዜና በተለያየ ምክንያት የመውደቅና የመነሳት ታሪክ ያጋጠመው መሆኑ ግልጽ ነው ።

እንግዲህ ያለፈውንና ያለውን ታሪካችንን መነሻ በማድረግ ወይንም ከአለፈው ታሪካችን በመማር ለአሁኑና ለወደፊቱ የቤተክርስቲያናችንን አገልጋዮች ማግኘት የሚቻለው ከአለውና ከሚቀጥለው ትውልድ ስለሆነ የአለውንና የሚቀጥለውን ትውልድ ለዚህ ዓላማ በትምህርት ማዘጋጀቱና ብቁ ማድረጉ ተወዳዳሪ ወይንም አማራጭ የማይገኝለት የቤተ ክርስቲያናችን ተቀዳሚ ሥራዋ መሆኑ ግልጽ ነው ። ይቀጥላል።



www.ethiopianorthodox.org

# መሠረተ ህይወት (የሕይወት መጀመሪያ)

መሠረት ማለት መጀመሪያ ማለት ነው ። አንድ ሕንፃ በሚሠራ ጊዜ አስቀድሞ በመሠረቱ ይጀመራል ። የሕንፃው አቋም የሚጠነከረውም መሠረቱ የጸና ሆኖ ሲመሠረት ነው ከሕንፃውም መሠረቱ እንዲቀድም ለእኛም የሕይወታችን መጀመሪያ ወይንም የመድኃኒታችን መሠረት ድንግል ማርያም ናት ።

ምክንያቱም በቀደመው ሰው አዳም የታጣው ልጅነት በእመቤታችን ድንግል ማርያም ተገኝቷልና ። የሕይወታችን መሠረት የሆነች ድንግል ማርያም ምክንያተ ድኂን ሆና ባትገኝ ኖሮ ዓለም ሊድን ባልቻለም ነበር። ነቢዩ ኢሳይያስ እንደተናገረው አሸናፊ እግዚአብሔር ንጽሕት ዘር ቅድስት ድንግል ማርያምን ከደጋጎች ሰዎች ኢያቄምና ሐና ባያተርፍልን ኖሮ ዘር መከር አጥተው እንደተጐዱ እንደ ሰዶም በሆነ እንደ ገሞራም በመሰልን ነበር ብሉአል ። ኢሳ.፩.፱.



የሕይወት መሠረት ድንግል ማርያም



የቀደመው ሰው አዳም የፈጣሪውን ትዕዛዝ ባለመጠበቅ ከክብሩ ተዋረደ ከቦታው ከገነት ወጣ በዚያን ጊዜም ስህተቱን እያሰበ በንስሐ ሆኖ ከማልቀስና ከማዘን በቀር ሌላ ሐሣብ አልነበረውም ። ለሰው መመለሱን እንጅ ጥፋቱን የማይፈቅድ የምሕረትና የርሕራኄ አምላክ የቀደመ ሰው አዳምን ንስሐውንና ኀዘኑን ተቀብሎ የተስፋ ቃል ኪዳን እንደሠጠው ይተረካል ። የቃል ኪዳኑም ፍሬ ነገር እንደ ቤተ ክርስቲያናችን አቆጣጠር አምስት ሺህ አምስት መቶ ዘመን ሲፈጸም ከልጅ ልጅህ ተወልጀ አድንሃለሁ ፣ የሚል ነበር ።

ይህ ሕይወታዊ የሆነ ተስፋ እንዴት እንደሚፈጸም በብሉይ ኪዳን ብዙ ትንቢት ተነግሯል ። ከተነገረውም ትንቢት እንዲህ የሚል ይገኝበታል ። "እግዚአብሔር በሴም ድንኳን ይደር ዘፍ.፱.፳፯ የሴም ድንኳን የተባለችም ለጊዜው የአብርሃም ድንኳን ብትሆንም ምሥጢሩ ግን ከነገደ ሴሜ የትውልድ ሐረግ ከተወለደ ከኢያቄምና ከሐና ከተወለደች ድንግል ማርያም የእግዚአብሔር ወልድን መወለድ ሲአስረዳ ነው ።

በሌላ በኩልም በታሪክ እንደሚነገረው ቅዱስ ኢያቄምና ቅድስት ሐና በብሉይ ኪዳን የታዘዘውን ሕግና ሥርዓት ጠብቀው ሲኖሩ ልጅ አልነበራቸውም መካን ሁነው ይኖሩ ነበር ። ለቤተ እግዚአብሔር መብዓ ለማቅረብ እንኳን ተከልክለው እያዘኑ ይኖሩ ነበር ።

ምክንያቱም እግዚአብሔር ቢጠላችሁ ነው እንጂ ቢወዳችሁማ ብዙና ተባዙ ብሎ ለአዳም በአዘዘው መሠረት ልጅ ይሠጣችሁ አልነበረምን ? እያሉ ካህናተ ኦሪቱ የመካናችን ሁሉ መብዓ ሊቀበሏቸው አልቻሉም ነበር ።

ግን የእግዚአብሔር ጸጋ ከእነሱ አልተለየምና አረጀን አፈጀን ብለው ተስፋ አልቆረጡም ነበር ። በንጹሕ ልቡና ሁሉን ለሚችል እግዚአብሔር ብጽአት ገቡ ። እሱም "ወንድ ልጅ ብንወልድ ወጥቶ ፣ ወርዶ ፣ አርሶ ፣ ነግዶ ፣ ይርዳን እንጂም ለቤተ እግዚአብሔር ምንጣፍ አንጣፊ ፣ ስዕለት አቅራቢ ሆኖ ያገለግላል ። ሴት ልጅም ብንወልድ ውሃ ቀድታ ፣ እንጨት ሠብራ ትርዳን እንጂም መጋረጃ ፈትላ ፣ መሶበ ፣ ወርቅ ሰፍታ ለቤተ እግዚአብሔር እድታገለግል እናደርጋለን" ብለው ቃል ገቡ ።

ይህ በዚህ እንዳለ የእግዚአብሔር መልአክ ቅዱስ ገብርኤል ደግ ልጅ ትወልዳላችሁ እላቸው በብሥራተ መልአክ በእግዚአብሔር ፈቃድ ነሐሴ ፯ ቀን ቅድስት ድንግል ማርያም ተፀነሰች በተፀነሰችም ጊዜ ገና ከእናቷ ቅድስት ሐና ማኅፀን ሳለች በተአምራት የአንዲት ሴት ዓይን እንዳበራችና



ምስለ ፍቁር ወልዳ

ቅድሶት ሐናን እየዳሰሱ በርከት ያሉ ሕመምተኞች ይፈወሱ ነበር ። የሞተ ሰውም እንዳስነሣች በታሪክ ተጽፏል ግን አይሁድ ያደረገችውን ታምራት በተመለከቱ ጊዜ ለምቀኝነት ኢያርፉም ና በጠላትነት ተነሣሡ ። ከዚህ ቀደም ከነዚህ ወገን የሆኑ ዳዊት ፣ ሰሎሞን ፃፃ ዘመን እንደ ስም አቅልጠው ፣እንደ ገል ቀጥቅጠው ገዝተው ነበር ። ደግሞ ከነዚህ እንደምን ያለይወለድ ይሆን፣ በማለት በምቀኝነት ተነሣሡ ። ስለዚህ የእግዚአብሔር መላክ ኢያቄምን አድባረ ሊባኖስ ይዝኃት ውጣ ብሎት ቅድስት ሐናን ወደ አድባረ ሊባኖስ ይዟት ወጣ ።

ቅድስት ድንግል ማርያም በአምስት ሺህ አራት መቶ ሰማንያ አምስት ዓመተ ዓለም ግንቦት አንድ ቀን ተወለደች። ሰሟንም ማርያም ብለው ሰይመዋታል ማርያም ማለትም ጸጋ ወሀብት ማለት ነው ። ለጊዜው ለእናትና ለአባቷ ጸጋ ሀብት ሆና ተሠጥታለችና ነው ። ፍጻሜው ግን ለክርስቲያኖች ሁሉ ከልጅዋ ከኢየሱስ ክርስቶስ እያማለደች ጸጋና ክብር ታሠጣለችና ።

ከዚህ ላይ ልናስተውለው የሚገባን በድንግል ማርያም መወለድ የሕይወታችን መሠረት እንደተመሠረተ ነው ። ምክንያቱም ሰውና እግዚአብሔርን አስታርቃ አቀራርባለች ።

ስለዚህ የሦርያው ሊቅ ቅዱስ ኤፍሬም ቅድስት ድንግል ማርያምን ባመሰገነበት ምስጋና በወርቅ መሰላል መስሎ ተናግሯል ። በመሰላል ሰዎች ከታች ወደ ላይ እንዲወጡበት ከላይም ወደታች እንዲወርዱበት ፣ ከእግዚአብሔር ጋር ለመዋሐዳችን ምክንያተ ሕይወት የሆነችን ድንግል ማርያም ናትና ።

በብሕንስም ኤጲስ ቆጶስነት የተሾመ አባ ሕርያቆስም በኖኅ መርከብ መስሎ አምስግኗታል ። የኖኅ መርከብ ለጊዜው ለስምንት ሰዎች ድኅነት ምክንያት ሁናለች ድንግል ማርያም ግን ከአዳም ጀምሮ ቁጥር ስፍር የሌላቸው ሕዝብና አህዛብን በባህረ ገሃነም ከመስጠም አድናለች ።

ምክንያቱም ኢየሱስ ክርስቶስ ከእርሷ በመወለዱ ዓለምን አድኗልና ።በሌላ በኩልም የደናግል መመኪያቸው ናት (ቅዱስ ጳውሎስ ብእሲ ወብእሲት አሐዱ አካል ብሎ እስከ አስተማረ ወንዶች በሴቶች ይመኩ እንደነበር ይተረካል።) ምክንያቱም ሔዋን ከአዳም ስለተገኘች እናንተ ከእኛ ተገኝታችኋል በማለት ነበር ። ግን ሔዋን ከአዳም ብትገኝም የዓለም መድኃኒት ኢየሱስ ክርስቶስ ከድንግል ማርያም ተገኝቷል ። ሞት በሔዋን ምክንያት በ.መጣም በድንግል

ወደ ፳ኛው ገጽ ዞሯል



www.ethiopianorthodox.org

# ዜና ሊቃውንት

አባ ይኄይስ ከአባታቸው ከአቶ ግለጤ አተሮ ከእናታቸው ከወ/ወለተ አረጋይ ይግለጡ በሸዋ ክፍለ ሀገር በመንዝና ግሼ አውራጃ በቀያ ገብርኤል ወረዳ ልዩ ስሙ ሶት አንባ በተባለው በ፲፱፻፲፪ ዓ.ም. መጋቢት ፳፯ ቀን ተወለዱ ዕድሜአቸው ለትምህርት ሲደርስ በቀያ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን ከሊቀ መዘምር ብርሃኑ ዘንድ ንባብና ዳዊት ከቃል ትምህርት ጋር አጠናቀው ተማሩ ቀጥለውም ዲቁና ተቀብለው በተወለዱበት ቤተ ክርስቲያን አንድ ዓመት ከአራት ወር ቀድሰዋል ከዚያም ወደወሎ ክፍለ ሀገር ሔደው ሐይቅ ኢየሱስ ሞአ (ደሴት) ገዳም ገብተው ከአባ ዘመደ መስቀል ዘንድ የሌሊትና የመዓልት ሰዓታትና መዝገብ ቅዳሴ ተማሩ ከዚያም ወደ ጐጃም ክፍለ ሀገር ሔደው ቅኔ ተምረዋል ዳግመኛም የቅኔ ሞያቸውን ለማስፋፋት ወደጉም ኢየሱስ ሒደው ከአለቃ ሣህሌ ቅኔ ከነአገባቡ ተምረው በቅኔ መምህርነት ተመርቀዋል ከዚህ በኋላ በዚሁ ክፍለ ሀገር ዲማ ጊዮርጊስ ከታላቁ ባሕታዊ ወልደ ማርያም ዘንድ የመጻሕፍተ ሐዲሳትን ትርጓሜ በሚገባ ተምረው በመምህርነት ተመረቁ ከዚያም ወደመርጦ ለማርያም ደብር ሔደው ከሊቁ ከአባ ቅንዋተ ኢየሱስ ዘንድ የውዳሴና የቅዳሴ ማርያም ትርጓሜ ከአምስቱ አዕማድ ሚሥጢር ጋር ከተማሩ በኋላ ከእኒሁ መምህር ዝማሬ መዋሥዕት አጠናቀው ተምረዋል ከዚያም ወደ ደብረ ሊባኖስ ገዳም መጥተው የምንኩስና ማዕርግ ከቆሞስ ኃይለ ማርያም ዘንድ ተቀብለው በመርሐ ቤቴ አውራ[ጃ] [ሰ]ኛ ሚዳ አቡነ መልከ ጼዴቅ ገዳም ፲ ዓመት የቅኔና የመጻሕፍተ ሐዲሳት ትርጓሜ መምህር ሁነው በማስተማር ብዙ [ሊ]ቃ መዘምራትን አፍርተዋል ከዚያም ፴፮ ዓ.ም ወደ አዲስ አበባ መጥተው [በገ]ነተ ልዑል ማርቆስ አንድ ዓመት ያህል እንደቆዩ ከብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ ዘንድ የቅስና ማዕርግ ተቀበሉ ቀጥሎም በ፴ ዓ.ም በምስካየ ኅዙናን ገዳ



አባ ይኄይስ ግለጤ እኒህ ነበሩ

ም መምህር ጽጌ የመጻሕፍተ ሐዲሳት መምህር ሁነው ሲያስተምሩ ስለነበር በኋላ ብፁዕ አቡነ ማርቆስ ተብለው ጳጳስ ሲሆኑ በምትካቸው በገነተ ልዑል

ማርቆስ የሚገኙት አባ ይኄይስ ይግለጤ ቢመደቡ የተሻለ ነው ተብሎ በምስካየ ኅዙናን መድኃኔ ዓለም ገዳም በ፵፫ ዓ.ም. ተመድበው የመጻሕፍተ ሐዲሳትን ትርጓሜ ያስተምሩ ጀመር ፳ ዓመትም እንዳስተማሩ በዚህ አጋጣሚ በእንገታቸውና ሽንጎበታቸው ላይ የቁስል ሕመም ስለአደረባቸው መጻሕፍተ ሐዲሳት የሚማሩት ተማሮች እየቀነሱ ስለሔዱ የሕፃናት መምህር ሁነው በሥጋዊና በመንፈሳዊ ትምህርት ሕፃናትን

እየኰተኰቱ ዳዊት በማስደገምና የዲቁና ሞያ በማስተማር ፴፮ ዓመት ሙሉ እስከ መጨረሻ ሕይወታቸው ድረስ ለቤተ ክርስቲያን ከፍተኛ አስተዋጽዖ አድርገዋል ።

በገዳሙ ማኅበራዊ ጸሎትም የሚሰለጥኑትን መነኮሳት በነበራቸው የአማርኛ ችሎታቸው ረድተዋል በትርፍ ጊዜአቸውም ከታወቁት ሊቅ ከአለቃ ወልደ ማርያም ዘንድ የባሕር ሐሳብ የቁጥር መጽሐፍ ተምረዋል ከዚህም ሌላ ምሥጢረ ዕፅዋት፥አማርኛ ቅኔ፡የዐባይ ባለቤት የሚባሉ ድርሰቶች ደርሰው አሳትመዋል ታላቁ ሊቅ አባ ይኄይስ ይግለጤ የዳዊትን መዝሙር የሚጸልዩት በቃላቸው ስለነበር በቀን ሁል ጊዜ ይዘልቁት ነበር አባ ይኄይስ የተቸገረ ሰው ሊለምን ያፈረ በገንዘብ ዕዳ ለተያዘ ዋስ ጠበቃ በመሆን በእጃቸው ገንዘብ ሲያጡ ተበድረው የሚለግሱ ቸር አባት ነበሩ ። አባ ይኄይስ የታመመ መጠየቅ ያዘነ ማፅናናት ተስፋ ለቆረጠ ማጠናከር የዘወትር ተግባራቸው ነበረ አባ ይኄይስ በአካባቢያቸው የሚኖረው ሕዝብ የሚወዳቸው ሁሉን በትክክል የሚወዱ ትዕቢት ምቀኝነት የሌላቸው ጾምና ጸሎት የዘወትር ተግባራቸው የሆነ ደግ አባት ነበሩ ነገር ግን ለሰው ልጅ ሞት የማይቀር በእግዚአብሔር ዘንድ የተወሰነ ስለሆነ የታመመ ሰው ለመጠየቅ ሐኪም ቤት ደርሰው ሲመለሱ በተወለዱ በ፹፭ ዓመታቸው ሐምሌ ፳፮ ቀን ፲፱፻፸፫ ዓ. ም. በመኪና አደጋ አርፈው በማግሥቱ ሐምሌ ፳፯ ቀን ፸፫ ዓ.ም በቀጨኔ መድኀኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን ወንድሞቻቸውና እኅቶቻቸው የሚያውቋቸው ምዕመናን ሁሉ በተገኙበት የቀብራቸው ሥነ ሥርዓት ተፈጽሞአል ።

አባ ገ/መስቀል ተስፋዬ ዘገነተ ማርያም



# ጾመ ፍልሰታ

የፍልሰታ ጾም በእመቤታችን ስም የሚጾም ሲሆን ፣ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሕግ መሠረት በዓመት ውስጥ ከሚጾሙት ሰባት አጽዋማት አንደኛው ነው ።

ይህ ጾም በሁለት ሱባኤ የተመደበ በመሆኑ ከቀኑ ማጠርና ከእመቤታችን ፍቅር ጽናት የተነሣ ትንሽ ትልቅ ፣ ሕፃን ሽማግሌ ሳይባል ምእመናን በሙሉ ሲጾሙት ይኖራሉ ጾመ ፍልሰታን እየጾሙ በየቤተ ክርስቲያኑ ቅዳሴ የሚያስቀድሱትን ጸሎት በመጸለይና በማናቸውም መንፈሳዊ አገልግሎት በመሳተፍ ረገድ መንፈሳዊ ዝንባሌ ያላቸውን ምእመናንና ብዛት የሚመለከቱ ሁሉ አድናቆታቸው እጅግ ከፍ ያለ እንደሚሆን የታወቀ ነው ። የሚያስደንቀው የታላላቅ ሰዎች ብቻ ሳይሆን የሕፃናቱም ሁኔታ ነው ምክንያቱም በሌላ ጊዜ ሻይ ሳይቀምሱ እስከ ሁለት ሰዓት መቆየት አቅቷቸው ወላጆቻቸውን ሲያስቸግሩ የሚታዩ ሕፃናት እስከ ዘጠኝ ሰዓት ድረስ ጾማቸውን ውለው በማስቀደስ ሥጋ ወደሙን ለመቀበልና ቅዳሴ ጸበልም ለመጠጣት ሲሽቀዳደሙ ማየት እውነትም የሚያስደንቅና የሚያስደስት ነው ።

በመሠረቱ ሰባቱ አጽዋማት ሁሉ እያንዳንዳቸው የሚጾሙበት ምክንያት እንዳላቸው ሁሉ ይህ ጾመ ፍልሰታ ወይም ጾመ ማርያም በመባል የታወቀው ስለእመቤታችን ፍቅር የምንጾመው ጾም ም ከነሐሴ ፩ እስከ ፲፭ ቀን ድረስ በየዓመቱ እንዲጾም የሆነበት በቂ ምክንያት አለ ። ይኸውም የአምላክ እናት የሆነችው እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም በዚህ ዓለም ፷፬ ዓመት በሕይወተ ሥጋ ከኖረች በኋላ ጥር ፳፩ ቀን አርፋለች ሐዋርያት የእመቤታችንን ሥጋ ለመቅበር ይዘዋት በሚሄዱበት ጊዜ ቅንዓትና ምቀኝነት ልማዳቸው የሆነ አይሁድ ምንጊዜም ከተንኮል አያርፉምና ልጅዋ ኢየሱስ ክርስቶስ ከሞተ በኋላ ተነሥቶ በመታየቱና የትንሣኤው ዜናም በመላው ዓለም በመሰማቱ ብዙዎች እየተከተሉት ነውና አሁንም እናቱንም ሞታ ተነሥታለች እያሉ ደቀ መዛሙርቱ በተጨማሪ እንዲያስቸግሩንና ብዙ ሰዎችንም እንዳያሳምኑ ከመቀበሯ በፊት እናቃጥላት በማለት አሲረው ተነሱ ሐሳባቸውንም ተግባራዊ ለማድረግ የእመቤታችንን ሥጋ የያዘውን አልጋ ለመያዝ በሞከሩ ጊዜ እግዚአብሔር እነሱን በተአምራት ቀጥቶ እመቤታችንን በገነት ካለች እፀ ሕይወት ሥር አኑሮ ከጥር ፳፩ እስከ ነሐሴ ፲፮ ቀን አቆይቷታል ።

ሐዋርያት በነዚህ ጊዜያት ሁሉ የእመቤታችን ሥጋ ስለተሰወራቸው እያዘኑና እየጸለዩ የቆዩ ቢሆንም በተለይ ከነሐሴ ፩ እስከ ፲፮ ቀን በጾምና በጸሎት ተወስነው ሱባኤ ይዘው እግዚአብሔርን በመለመናቸው ሱባኤውን በጀመሩ በ፲፮ኛው ቀን የእመቤታችንን ሥጋ ለማየት በቅተዋል እንደሕጋቸው አጥበው ገንዘው ከቀበሯት በኋላ በ3ኛው ቀን ተነሥታ አርጋለች ይህም በጾምና በጸሎት የተገኘ ጸጋና ክብር በመሆኑ የሐዋርያትን ፈለግ በመከተል ምእመናን ሁሉ እነዚህን ዕለታት ስለእመቤታችን ክብር ብለው በእመቤታችን ስም የፍልሰታን ጾም በየዓመቱ በትጋትና በሕብረት ሲጾሙ ይታያሉ ።

በፍልሰታ ጾም ባሕታውያን ከእህል ተለይተው ሥር ምሰው ቅጠል በጥሰው ያንን ብቻ ቀምሰው በታላቅ ቀኖና የሚጾሙ ሲሆን በየገዳማቱ የሚገኙት መኖኮሳትና በከተማም ሆነ በገጠር የሚኖሩ መንፈሳውያን አባቶች ደግሞ በቀን አንድ ጊዜ ጥሬ እየቆረጠሙ ውኃ እየጠጡ በመንፈሳዊ ስሜት ይጾሙታል ።ሌሎችም እንደየደረጃቸው ሻይ ፣ ቡና ሳይሉ እስከ ዘጠኝ ሰዓት ድረስ ጦማቸውን ውለው በማስቀደስ በአጠቃላይም ሥጋ ፣ ቅቤና እንቁላልን የመሳሰሉ አልሚ ምግቦችንም ከመመገብ ተከልክለው በዚህ ሱባኤው ውስጥ ሥጋቸውን ቀጥተው ለነፍሳቸው በማደር የሚያደርጉት መንፈሳዊ እንቅስቃሴ በቀላል የሚገመት አይደለም ። በአጠቃላይ በጾመ ፍልሰታ በየቀኑ በየቤተ ክርስቲያኑ የሚያስቀድሱት ምእመናን ብዛት ቁጥር እጅግ ከፍ ያለ በመሆኑ አገልግሎቱም በዚያው መጠን ለየት ያለ ቀልጣፋ አሠራርና ፕሮግራም ሊኖረው የሚገባ ነው ።

ለምሳሌ ከሥራ ወጥተው ባላቸው የእረፍት ጊዜ ውስጥ አስቀድሰው ለመመለስ የሚፈልጉ ምእመናን ብዙ በመሆናቸው ሰባት ካልሞላ ከቅዳሴ አንገባም ያለዘጠኝም አንወጣም ይህ ከሆነ ልማድ ይፈርሳል ሥርዓት ይፋለሳል የሚሉ ካህናት ቢኖሩ የምእመናንን መንፈሳዊ ፍላጎት መግታትና ተስፋም ማስቆረጥ መሆኑን ሊረዱት ይገባቸዋል ። በጾመ ፍልሰታ የቆራቢዎች መጠን በጣም ብዙ በመሆኑ ሥጋ ወደሙን ለማቀበልና ቅዳሴ ጸበልም ለማዳረስ የሚወስደው ጊዜ በዚያው መጠን የሚረዝም መሆኑ የታወቀ ነው ። ስለሆነም በአዲስ አበባ ባሉ አድባራት ይኸው ችግር ተጠንቶ ስለታወቀ ፣

፩ኛ/ በ፮ ሰዓት ተኩል ቅዳሴ ገብተው ልክ በ፰ ሰዓት በማጠናቀቅ ጊዜውን እያሻሻሉ ናቸው ።

፪ኛ/ ሴቶችና ወንዶች ሕፃናትና ሽማግሌዎች የሚቆርቡበት ጊዜ በሺፍት (በየተራ) እንዲሆን በመሆኑ ጊዜን ለመቆጠብ ረድቷል ።

፫ኛ/ ሥጋ ወደሙን በሁለት በኩል በማቀበል የሚደረገው ቀልጣፋ አሠራር ጊዜን ለመቆጠብ እንዳስቻለ ተረጋግጧል ። ስለዚህ ይህ አሠራር እንዲቀጥል ሆኖ ከዚህ የተሻለ ዘዴም ከተገኘ ቢታከልበት መልካም መሆኑን ለመጠቆም እንወዳለን ።

ሊደረጉ የሚገባቸው ጥንቃቄዎችና



www.ethiopianorthodox.org

ሊታረሙ የሚገባቸው ስህተቶችም ስላሉ ጠቅላላው ምእመናን በሚደረገው እርማትና በሚወሰደው እርምጃ ሁሉ መተባበር ይኖርባቸዋል ።

ለምሳሌ ሕፃናት የሥጋ ወደሙን ምስጢር በሚገባ ስለማይረዱ በሚቀርቡበት ጊዜ ጥንቃቄ ሳይወስዱ በልማድ ብቻ ለመቁረብ የሚመጡ ሊኖሩ ይችላሉ ስለዚህ እነዚህን ሕፃናት በማስተማር ረገድ ከፍተኛ ኃላፊነት ያለባቸው ወላጆች ናቸው ። ካህናትም ፕሮግራም በማውጣት ሰዓት መድበው ከመቁረባቸው በፊት ለተወሰኑ ጊዜያት ትምህርት ቢሰጧቸው በመንፈስ የዳበረ አእምሮ እንዲኖራቸው ይረዳቸዋል ከዚህም ጋር ቅዳሴ ፀበል በሚሰጥበት ጊዜ የሚታየው ትርምስ እንዲቀር ምእመናን ቅደም ተከተላቸውን ጠብቀው በተራ መቀበል ያለባቸው መሆኑን ሊዘነጉት አይገባም ይህ ካልሆነ ግን በትርምስ የሚባክነው ጊዜ እየበዛ ከመሄዱም በላይ ለአሠራር አመቺ ሳይሆን ሲቀር ልውካኑ ያመጡትን በግርግር ስለሚመልሱት የሚፈለገውን ቅዳሴ ፀበል ለማግኘት ያለው ዕድልም ጠባብ ስለሚሆን ለሁሉም ነገር ሥነ ሥርዓት ቢኖረው ጥሩ ነውና ሊታሰብበት ይገባል ።

ኢሳይያስ ወንድማገኘሁ

# የጽድቅ ፍሬ

“የጽድቅ ፍሬ ሰላምን ለሚያደርጉ ሰዎች ሁሉ በሰላም ይዘራል ” /ያዕ ፫፥፲፰/ ። በመሠረቱ ጽድቅ በእምነት አማካኝነት ወደ ሰዎች የሚተላለፍ የእግዚአብሔር የባሕርይ ገንዘብ ነው ። ጽድቅን ማግኘት የሚችሉም አካሄዳቸውን ከእግዚአብሔር ጋር ያደረጉ ዕውነተኞች አማኞች ብቻ ናቸው ዘፍጥ ፮፥፰-፱

ሐዋርያ ያዕቆብ “ጽድቅን” በምድር ላይ በሚዘራ ፍሬ መስሎ ሲናገር ይህ የጽድቅ ፍሬ በሰላም የሚዘራው ለሰላም ሰዎች መሆኑን ያበሥራል የጽድቅን ፍሬ በምድር ላይ የዘራ ራሱ የጽድቅ ባለቤት የሆነ ክርስቶስ ነው ። የርሱ ተከታዮች የሆኑ የወንጌል መምህራን ይህኑ የጽድቅ ዘር ቡቃያ ተከባክበው ለፍሬ እንዲደርስ የመጠበቅ ኃላፊነት አለባቸው ፍሬውን የሚያበዛና የሚባርክ ግን እግዚአብሔር ነው ፩ ቆሮ ፫፥፭-፱/

ይህም የጽድቅ ፍሬ የሚዘራበት መሬት የምዕመናን ልብ ነው ። ታዲያ የብዙዎች አማኞች ልብ ሁሉ የተለያየ ደረጃ አለው ። ይኸውም አንዳንዱ እንደአለት የጠነከረ ጢንጫ ሲሆን ሌላው በጥርጣሬና በከንቱ የምኞት እሾህ የተከበበ ሆኖ በሕይወታቸው የሚዘራውን ቃል አንቆ ያለ ፍሬ ሊያስቀረው እንደሚችል ጌታ ራሱ በወንጌል ተናግሮአል ። /ማቴ ፲፫፥፲፰-፳፪/

ይሁን እንጂ በለሰለሰ መልካም መሬት የተመሰለ ንጹሕ ልብ አለ ። “እርሱም ቃሉን ሰምቶ ማስተዋል የሚችል ነው ። እርሱም ብዙ ፍሬ ያፈራል አንዱ ባለመቶ አንዱ ባለስድሳ ሌላውም ባለ ሰላሣ ፍሬ ይሆናል ። /ማቴ ፲፫፥፳፫/

እንዲህ ያለውን ልብና አእምሮ ለማግኘት የጽድቅ ባለቤት የሆነውን እግዚአብሔርን በጸሎት መለመን ይገባናል ። ጸሎታችን ቅድመ እግዚአብሔር ደርሶ መልስ ማግኘትም እንድንችል ፍጹም የሆነ የእምነት ጽናት እንዲኖረን የስፈልጋል “ጻድቅ በእምነት ይኖራል” ተብሎ ተጽፎአልና /ዕን ፪፥፬/

ከእምነትም ጋር የተስተካከለ ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር ያስፈልጋል የበጎ ሥነ ምግባር ዋና መሠረቱም ፍጹም እምነት ነው ። የሥነ ምግባር መንደልና የሞራል ስብራት የሚመጣውም ከእምነት ብሎን መላላት ነው ። “ሃይማኖትስ መሠረት ይዕቲ ወካልዓኒሃ ሕንፃ ወንድቅ እሙንቱ” ሃይማኖት መሠረት ስትሆን እርስዋን ተከትለው የሚመጡ በጎ ምግባራት እንደ ጣራና ግድግዳ መሆናቸውን ሊቃውንት በምሳሌ ያስረዳሉ። “ሃይማኖት ይቅደመኝ ምግባር ይከተለኝ” እንዲሉ የጽድቅ ፍሬም የሚገኘው ከነዚህ ከሁለቱ ነገሮች ማለትም ከእምነትና ከበጎ ምግባር ተባብሮ መገኘት የተነሣ ነው ።

በዕርግጥ ሰው በተፈጥሮው የደካማነት ባሕርይ እንዳለበት ራሱ እግዚአብሔር ከተናገረው የሚበልጥ ሌላ ምስክር አያስፈልገንም እርሱም “የሰው ልብ ከተናሽነቱ ጀምሮ የክፉ ነው የሚል ቃል ይገኝበታል ” ታዲያ በምን አቅሙ የጽድቅ ባለቤት መሆን ይችላል? ቢባል ይኸው ደካማነቱ ታውቆ በክርስቶስ ደም የተዋጀ ስለሆነ በራሱ ሰብአዊ ጥረት ሳይሆን በእምላካዊ ፈቃድ የመዳን ጸጋ ስለተሰጠው ጽድቅን አግኝቷል ። “ታዲያ እግዚአብሔር ያጸደቀውን ማን ሊኮንነው ይችላል ? ” ስለዚህም በሰው ሕይወት የተዘራው የጽድቅ ፍሬ በእምነት ለሚቀበለው ሁሉ የመንፈስ ሰላምን ይሰጣል የእግዚአብሔርን ቃል የሚሰማና የታዘዘውን የሚፈጽም ዕውነተኛ አማኝ ሁሉ የሥነ ምግባር መሰናክል በሚያጋጥመው ጊዜም በንስሐ የመታደስ ዕድል ተሰጥቶታል

“ጻድቅ ብእሲ ሰብኤ ይወድቅ ወሰብእ ይትነሣእ ጻድቅ ሰው ሰባት ጊዜ ቢወድቅ እንኳ ሰባት ጊዜ ተነሥቶ በዓላማው ጸንቶ ለመቆም ይችላል ሲል ሰለሞን በምሳሌው የተናገረውም ስለዚህ ነው /ምሳሌ ፳፬፥፲፮/

አሁንም የጽድቅን ሥራ ከመሥራት እንታክት” እስመ በጊዜሁ ነዐርር ወቅቱ ሲደርስ መሰብሰብ እንችላለንና” ሲል ሐዋርያ ጳውሎስ የተናገረውን መሪ ቃል በማስታወስ በክርስቶስ ጸጋ ለተጠራንበት ጽድቅ እንድንበቃ በእምነት ጸንተን እንቁም ። በላታ ወ/ጊዮርጊስ ወ/ ዮሐንስ ሥነ ምግባር በተሠኘው መጽሐፋቸው ሲገልጡ “የሥነ ምግባር ጉድለት እንደ ቆዳ በሽታ የሚቆጠር ሲሆን የሃይማኖት ጉድለት ግን የልብና የኩላሊት በሽታ ስለሆነ ከዚያ ይልቅ ይህ ይከፋል” ብለዋል ። ይህም ከሆነ የምግባርን ስብራት መጠገን የምንችልበት ተነሳሒ ሕይወትና ፍጹም እምነት እንዲኖረን ሁሉን ቻይ የሆነ ሕያው አምላክ በቸርነቱ ይርዳን በክርስቶስ ቃል የተዘራው የጽድቅ ፍሬ ለዘለዓለም ይኑር”

አሜን

ቄ/ መክብብ አጥናው



# ከበለስ በታች አየሁህ

ይህ ቃል የተነገረ ከጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሲሆን የተነገረ ለናትናኤል እንደሆነ ተገልጾአል ። ዮሐንስ ፩ ቁጥር ፵፱ ለነገሩም መነሻ ምክንያት የሆነው ፊሊጶስ ናትናኤልን አገኘውና ነቢያት ትንቢት የተናገሩለትንና ነቢዩ ሙሴ በኦሪት ስለ እሱ የጻፈለትን የናዝሬቱ ኢየሱስን አገኘነው ብሎ በነገረው ጊዜ ናትናኤል ሊአምንና ሊረዳለት አልቻለም ። ፊሊጶስ ግን ቀደም ብሎ ክርስቶስ አግኝቶት እንዲከተለው ጠይቆት ስለነበረ ኢየሱስ ክርስቶስ መሆኑን እጅግ አውቆና ተረድቶ ነበረ ። ናትናኤል ግን ሊረዳ ባለመቻሉ ለመሆኑ ከናዝሬት ደግ ሰው ይወጣ ዘንድ ይቻላልን አለ ። ናትናኤል ይህን የተናገረ የክርስቶስን ወደ ዓለም መምጣት ተጠራጥሮ ሳይሆን ናዝሬት የተራዎች ሰዎች መኖሪያ መሆኗን ስለሚአውቅ ነው ።

እየደጋገመ ቢነግረውም ስለ አልተረዳለት እንግዲህ ክርስቶስ መሆኑንም አለመሆኑንምና እና እይ ብሎ ወደጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ይዞት ሄደና ገና ከሩቅ ሲመጣ ናትናኤልን ባየው ጊዜ ክርስቶስ እንዲህ አለው ። በእውነት ተንኮል የሌለበት እስራኤላዊ እነሆ ብሎ ስለእሱ መሰከረለት ። እስራኤል ማለትም የእግዚአብሔር ወገን ማለት ነው ።

ናትናኤልም ይህን ጊዜ እጅግ ተደነቀና በአንክሮ ወዴት ታውቀኛለህ አለው ገና ፊሊጶስ ሳይጠራህ ከበለስ በታች ሳለህ አየሁህ ብሎ መለሰለት ።

እዚህ ላይ ልናስተውለው የሚገባ ሰዎች በዓይናቸው ያዩትንና በጆሮአቸው የሰሙትን ይመሰክራሉ እንጂ ያላዩትንና ያልሰሙትን ሊአውቁት አይችሉም ።

ክርስቶስ ግን የባሕርይ አምላክ እንደ መሆኑ ከእሱ ያልተገኘ እሱ የማያውቀው ከእሱ የተሠወረ ፍጥረት የለምና። ፍጥረቱን ሁሉ በእያሉበት ቦታ እንደሚመለከታቸው ፊሊጶስ ሳይጠራህ ከበለስ በታች አየሁህ ያለው ቃል የባህርይ አምላክነቱን ያስረዳል ። በሌላ በኩልም ከበለስ በታች አየሁህ ማለት በኃጢአት ጥላ ሥር የተጋረደውን ሰው ሁሉ ኃጢአቱን እንደሚአውቅበትና ከእሱም እንደማይሠወር ሲአስረዳ ነው ።

በአንድ በኩልም አንድ ሰው የሌላውን ሰው መልኩን ቢአውቀው ጠባዩንም ከሞላ ጐደል ቢአውቀው በልቡናው ያለውን ሐሳብ ከቶ ሊአውቀው አይችልም ። እግዚአብሔር ግን ሰውን ከመፍጠሩ አስቀድሞ ግብሩን ያውቀዋልና ። እምቅድመ ይፍጥር ለአዳም የእምርግብር አዳምን ከመፍጠሩ አስቀድሞ ግብሩን ያውቀዋል ። ተብሎ ተጽፎአልና ስለዚህ ናትናኤል ከዳት ሸንገላ የሌለበት በመሆኑ ከፍጹምነት ደረጃ እንዲደርስ መስክርለታል ።

እንግዲህ ሐዋርያው ናትናኤል በአንድ ወገን ስምዖን ቀነናዊ ይባላል ። ናትናኤል ማለት ሐብተ እግዚአብሔር ሲሆን ስምዖን ማለትም እግዚአብሔር ሰማኝ ማለት ነው ቀነናዊ የቃና ሰው የትውልድ ሐገሩም የገሊላ አውራጃ የሆነች ቃና ናት ።

ሄሮድስ የገሊላን ሕፃናት በአስፈጀ ጊዜ በዚያን ጊዜ ናትናኤል ገና በሕፃንነት ደረጃ ስለነበረ እናቱ ከበለስ በታች ሠውራው እንደ ነበረና በእግዚአብሔር ፍቃድ ከሄሮድስ መቅሠፍት እንደዳነ በመጽሐፈ ስንክሳር ይነገራል ። እንግዲህ ስንመለከተው ናትናኤል ከበለስ ቅጠል በታች ተጠልሎ በነበረበት ወቅት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም በዚያን ጊዜ የገሊላው ሄሮድስ ሊአስገድለው ያስፈልገው ስለነበረ በእመቤታችን ድንግል ማርያምና በሽማግሌው ዮሴፍ አማካይነት ወደ ግብፅ ሀገር እንደ ተሰደደ ይነገራል ። ከበለስ በታች አየሁህ የሚለው ንባብም በግብፅ ሀገር ሆኖ በዓይነ ሥጋ ተመለከተው ማለት ሳይሆን በባሕርይ አምላክነቱ እንደተመለከተውና እንደ አዳነው ያስረዳል ።

አምላክነቱን ቦታ አይወስነውምና የተሠወረውንም እንደሚአውቅ ሲአስረዳ የሰውን ሐሳብ ከመሆኑ አስቀድሞ ያውቃል ተብሎ ተፅፎአልና ።

ናትናኤልም ፊሊጶስ ገና ሳይጠራህ ከበለስ በታች አዩየሁህ ብሎ የተሠወረውን አውቆ ስለ ነገረው እጅግ ተደነቀና መምህር ሆይ አንተ የእግዚአብሔር ልጅ ነህ የእሥራኤልም ንጉሥ ነህ አለ ። እሱም ከበለስ በታች አየሁህ ስለአልሁህ አመንህን ገና ወደፊት ከዚህ የሚበልጥ ተአምር ታያለህ አለው ።

ሐዋርያው ናትናኤል በጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለሐዋርያነት ከተመረጠ በኋላ ጌታችንን ተከትሎ ሦስት ዓመት ከሦስት ወር የተሰጠውን የወንጌል ትምህርት አብሮ ይሳተፍ በነበረበት ወራት ልዩ ልዩ ደጋግ ተአምራትን እን



www.ethiopianorthodox.org

# የአባ ኃይለ መለኮት አጭር የሕይወት ታሪክ

በመማርና በማስተማር በውደተ ገዳማትና አድባራት ገድላቸውን የፈጸሙት ፲፱፻፴፮ ዓመታት የሆናቸው መሆኑን በሕይወተ ሥጋ ሳሉ ያስመዘገቡት ቃል ያስረዳል ባሕታዊ አባ ኃይለ መለኮት ነቢየ ልዑል ሚያዝያ ፲፪ ቀን ፲፱፻፸፯ ዓ.ም ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለዓለም ቤዛ ሆኖ በተሰቀለበት በበዓለ ስቅለት ዕለት ዓርብ ከጠዋቱ በ፪ ሰዓት ከዚህ ዓለም ፃማና ድካም እንዳረፉ ለቅዱስ ፓትርያርኩ ተነግሮአቸው ቅዱስነታቸውም ብፁዕ አቡነ ዮሴፍን በሥርዓተ ቀብሩ እንዲገኙ አዘው የአባ ኃይለ መለኮትም ቅዱስ አስከሬናቸው በገነተ ጽጌ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን እስከ ፲ ሰዓት ከቆየ በኋላ ብፁዕ አቡነ የሴፍ የግብአተ መሬቱን ጸሎት አድርሰው በመልአከ ገነት ገዳሙ ወ/ ገብርኤል አማካኝነት ብዙ መነኮሳትና ባሕታውያን ቀሳውስትና ዲያቆናት ለበዓለ ስቅለቱ የተሰበሰቡት ምዕመናን በሙሉ ስለ አባትነታቸው እያለቀሱ በገነተ ጽጌ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓተ ቀብሩ ተፈጽሟል ።

---

ደተመለከተና እንደተረዳ ታውቆአል ። ስለዚህ ነው ከዚህ የበለጠ ተአምር ታያለህ ብሎ ያስገነዘበው እንዴአውም ከግዙፋን ፍጥረታት ይልቅ ረቂቃን መላእክትን ከወደሰማይ ሲወጡና ሲወርዱ ታያላችሁ ብሎ አስተምሮታል ። ዮሐንስ ፩ ቁጥር ፶፪ እንግዲህ በተፈጥሮ ረቂቃን የሆኑ መላእክትን ከማየት የበለጠ አስደናቂ ተአምር የለም እኛም እንደሐርያው ናትናኤል በክርስቶስ ትምህርት አምነን ክርስቶስን ክተከተል ነው ማለት በሥራ ከመሰልነው በዚህ ዓለም ካለው የአረቦኑ ክብር የበለጠና ተወዳዳሪ የማይገኝለት ሰማያዊ ክብርን ሰማያዊ ሕይወትን እንድንጐናጸፍ እናምናለን ።

መምህር ኪዳነ ማርያም አየለ

የሕይወት ታሪካቸውም እንደሚከተለው ነው አባ ኃይለ መለኮት በጐንደር ክፍለ ሀገር በደብረ ታቦር አውራጃ በእስቴ ወረዳ በምትገኘው ማኅደረ ማርያም ከአባታቸው መምህር ነቢየ ልዑል ሥዩምና ከእናታቸው ወይዘሮ አስናቀች ለማ በ፲፰፻፶ ዓ.ም ተወለዱ በተወለዱ በ፯ ዓመታቸው በወቄጣ ማርያም ደብር ከነበሩት መምህር ገብረ ኢየሱስ ዘወንጌል ትምህርት ጀምረው ንባብ ዳዊት ውዳሴ ማርያም ወዘተ ከተማሩ በ



አባ ኃይለ መለኮት እኒህ ነበሩ

ኋላ በዚያው ወረዳ ወደሚገኘው አንዳ ቤት ሄደው ሌባ መጣያ መካነ ሥላሴ ከሚባል ደብር ከመሪጌታ በቃ ጥበቡ ጾመ ድጓ ምዕራፍ በሚገባ ተምረዋል። በ፲፰፻፸ ዓ.ም ወደ ጐጃም ክፍለ ሀገር ሄደው በዋሸራ ማርያም ከመምህር ምሥራቅ ኢያሱ ቅኔ ከነአገባቡ ተምረው ለማስተማር ሲበቁ ወደ ጐንደር ክፍለ ሀገር በመመለስ ጋይንት አውራጃ በምትገኘው ቤተ ልሔም ከመምህር ጌራወርቅ ወልደ ጊዮርጊስ ድጓ አስመስክረዋል ያስመሰከሩበትም ዘመን በ፲፰፻፸፮ ዓ.ም ነው ።

፲፰፻፸፰ ዓ.ም. ወደ ዙርበምባ ሄደው ከመምህር ተክሥተ ብርሃን ዘፈረ ወርቅ ዝማሬና መዋሥዕት ተምረው በመምህርነት ተመርቀዋል ። በ፲፰፻፹፪ ዓ.ም በጐንደር ከተማ በዓታ ደብረ ኃይል ከመምህር ልሳነ ወርቅ ገብረ ሥላሴ አቋቋም ተምረው አስመስከረዋል ። በ፲፰፻፺፪ ዓ.ም ሁለተኛ ወደ ጐጃም ክፍለ ሀገር ሄደው በደብረ ድማኅ ቅዱስ ጉዮርጊስ ብሉያትን ከመምህር አብርሃም ኃይለ ኢየሱስ ሐዲሳትን ከመምህር ዕዝራ ወልደ ሰንበት ተምረው ለማስተማር በቅተዋል ። ከዚያም ወደ ኤርትራ ክፍለ ሀገር ሄደው በደብረ ቢዘን አቡነ ፊልጶስ ገዳም መጽሐፈ ሊቃውንትንና መጽሐፈ መነኩሳትን ተምረው ከፈጸሙ በኋላ እንደ ገና ወደ ጐጃም ክፍለ ሀገር ሄደው ፲ ዓመታት ቅኔ ካስተማሩ በኋላ ወደ ጐንደር ሀገረ ስብከት በመሄድ በደብረ ታቦር አውራጃ 15 ዓመታት ሙሉ ዜማ በማስተማር ብዙ ደቀ መዛሙርቶችን በትምህርት አሰልጥነው ለቤተ ክርስቲያናችን አበርክተዋል ።

ከዚያም ወደ ጐጃም ክፍለ ሀገር ሄደው በግሼ ዓባይ በአቡነ ዘርአ ቡሩክ ቤተ ክርስቲያን በመቃብር ቤት ለ፯ ዓመታት በብሕትውና ዘግተው እንዳሉ ርግብ በራሳቸው ላይ አርፋባቸዋለች ከዚህ በኋላ በመላው ኢትዮጵያ እየተዘዋወር ክአስተምር የሚል አምላካዊጥሪ ስለደረሳቸው በከተማ በገጠር በበረሃ በአድባራትና ገዳማት እየተዘዋወሩ ማስተማራቸውን ቀጥለዋል ።

አባ ኃይለ መለኮት ነቢየ ልዑል

በ፲፰፻፶፮ ዓ/ም ሲመተ ዲቁናን ከአቡነ ሰላማ

በ፲፱፻፫ ዓ.ም መዓርገ ምንኩስናን ከመምህር መልከ ጼዴቅ ቀጸላ ጊዮርጊስ በደብረ ዳሞ አቡነ አረጋዊ ገዳም ተቀብለዋል ።

በ፲፱፻፬ ዓ.ም መዓርገ ቅስና ን ከአቡነ ማቴዎስ


በ፲፱፻፳፮ ዓ.ም መዓርገ ቁመስናና ኩርስና ከአቡነ ቁርሎስ ተቀብለዋል ።

ለ/ ምዕመናንን በማስተባበር

ያሠሯቸው አብያተ ክርስቲያናት

፩/ በጐጃም ክፍለ ሀገር በሰከላ ውስጥ ሳንገብ ቅዱስ ሚካኤልን ቤተ ክርስቲያን ፪/ በወሎ ክፍለ ሀገር ደብር ቅዱስ የአቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ቤተ ክርስቲያንን ፫/ በዚሁ ክፍለ ሀገር ደብረ ጎሀ ጽባሕ ተክለ ሃይማኖት ቤተ ክርስቲያንን ፬/ በዓባይ ዳር በአማራ ሳይንት ድንቻ ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያንን ወዘተ ናቸው ።

ባሕታዊ አባ ኃይለ መለኮት እንደ ሐዋርያት ራበኝ ጠማኝ በረደኝ ሳይሉና



አባ ኃይለ መለኮት እየዞሩ ከጸለዩባቸው ና ካስተማሩባቸው አንዱ አኩስም ጽዮን

ሳይሳቀቁ ለእግራቸው ጫማ ሳያደርጉ በእጃቸው በትር ሳይዙ ጥሪትና ቁሪት ሳይኖራቸው ብዙውን ዘመናት በማስተማር ያሳለፉት ሲሆን ከዚያ የተረፉትን ዘመናት ደግሞ በውደተ ገዳማትና አድባራት ሽኝተዋቸዋል አባ ኃይለ መለኮት በእግራቸው እየዞሩ ከተሳለሟቸውና ከጸለዩባቸው ቅዱሳት መካናት በከፊል ።

ግሸን ማርያም ፣ አክሱም ጽዮን ፣ ጣና ቂርቆስ ፡ ተድባበ ማርያም ፡ መርጡለ ማርያም ፣ ደብረ ቢዘን ፣ ቅዱስ ላሊበላ ፡ ማኅበረ ሥላሴ ገዳም ፡ ዋልድባ ገዳም ፣ ደብረ ሞጊና ገዳም ፣ ጐንድ ተክለ ሃይማኖት ገዳም ፣ ደብረ ዳሞና የተሰአቱ ቅዱሳን ገዳም ፣ ምስካበ ቅዱሳን፣ አዘሎ ደብረ ኩሩብ ፣ ዳጋ እስጢፋኖስ ዑራ ኪዳነ ምሕረት ፣ ጣና ክርስቶስ ሠምራ ደብረ ሊባኖስ ፣ ዝቋላ ገዳም አሰቦት ገዳም ፣ የ፯ቱ ከዋክብት ቅዱሳን ገዳም ፣ ሀገረ ናግራን ጉራይሌ ወዘተ ናቸው ።

ከ፲፱፻፶፪ ዓ.ም ጀምሮ በአዲስ አበባ ከተማ በአባ መሸበክንቱ ሐዋርያ ስብሳቢነት በማኅበረ ሕይወት ቅድሥት ሥላሴ ማኅበር ትምህርት ቤት ግቢ ውስጥ በአታቸውን አድርገው በ፲፬ቱ አህጉረ ስብከትና በአዲስ አበባ አድባራትና ገዳማት እየተዘዋወሩ በማስተማርና በመጸለይ ሲኖሩ እስከ ዕለተ ሞታቸው የመንፈስ ቅዱስ ልጃቸው የሆኑት

ከተጠቀሱት ገዳማት ሌላ በእግራቸው ወደ ኢየሩሳሌም ተጉዘው ከቦታው በመድረስ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተወለደበትን ቤተ ልሔምን ያደገበትን ናዝሬትን ብርሃነ መለኮቱን የገለጸበትን ደብረ ታቦርን የተሰቀለበትን ቀራንዮን የተቀበረበትን ጎልጎታን የተጠመቀበትን ዮርዳኖስንና ሌሎችንም በኢየሩሳሌም የሚገኙትን ቅዱሳት መካናት ጐብኝተውና ተሳልመው ጸልየው ወደ ሀገራቸው ወደ ኢትዮጵያ ተመልሰው እየዞሩ የማስተማር ተግባራቸውን ቀጥለዋል ።


መምህር ፍሬው ጥሩነህ ምግብ በማዘጋጀትና ልብሳቸውንም በማጠብ በቅንነትና በትህትና ለብዙ ጊዜ ረድተዋቸዋል ። ብፁዕ ወቅዱስ በቡነ ተክለ ሃይማንትም በልዑል እግዚአብሔር ፈቃድና ምርጫ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ ከሆኑበት ጊዜ ከ፷፰ ዓ.ም ጀምሮ በልዩ አባታዊ ችሮታቸው ለአባ ኃይለ መለኮት ለሠርከ ኅብስታቸው የሚሆን የገንዘብ ዕርዳታ እስከ ዕለተ ሞታቸው ድረስ ከመርዳታቸውም ሌላ በጠና በታመሙበት





www.ethiopianorthodox.org

በ፲፱፻፸፬ ዓ.ም ወደ ሐኪም ቤት ገብተው እንዲታከሙ አድርገው ሕመማቸው ተሽሎአቸው ተመልሰዋል ። ከ፲፱፻፸፬ ዓ.ም እስከ ፲፱፻፸፮ ዓ.ም ድረስ ከሁለት ዓመት በላይ በዕርግናና በሕመም ምክንያት በቤታቸው ውለው ነበር ።



ባሕታዊ ኃይለ መለኮት በዝቋላ አቡነ ገ/መንፈ ቅዱስ ገዳምም አልፀዋል

እኚህ ታላቅ አባት ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በጸጋ ዘነሣዕክሙ በጸጋ ሀቡ ዋጋ ሳትከፍሉ የተማራችሁትን ዋጋ ሳትቀበሉ አስተምሩ ያለውን ቃል መሠረት በማድረግ አቀበቱን ወጥተው ቁልቁለቱን ወርደው በረሃውን አቋርጠው ወንዙን ተሻግረው ደከመኝ ታከተኝ ብለው ሳይመረሩና ጉልበታቸውን ሳይቆጥቡ ለብዙ ሕዝብ የወንጌልን ቃል አስተምረዋል ። በርከት ያሉ ደቀመዛሙርቶችንም በሚገባ አስተምረው ለቤተ ክርስቲያናችን አገልግሎት ብቁ አድርገው አስረክበዋል። እኚህ ታላቅ ባሕታዊ ከዚህ ዓለም በሞት ሲለዩ ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ከፍ ያለ ኀዘን ቢሰማትም መሬት ነህና ወደ መሬት ተመለስ በሚለው አምላካዊ ቃል ሥጋን ለለበሰ ሁሉ ሞት የማይቀር በመሆኑ ለነፍሳቸው ዘለዓለማዊ ዕረፍትን እንዲሰጣት ልመናዋን ወደ እግዚአብሔር ታቀርባለች ።

አባ አልዓዛር አድኃነ

# መሠረተ ሕይወት ...

አገጽ ፱ የዞረ

ማርያም ሕይወት ተገኝቷልና።በሔዋን ምክንያት ከገነት ቢወጡም ፡ በድንግል ማርያም ገነት መንግሥተ ሰማይ ገብተዋልና ። ርእሱን መሠረተ ሕይወት ያልሆነውም ስለዚህ ነው ።

ከተወለደች በኋላም ሦስት ዓመት ከእናት ከአባቷ ቤት የኖረች ስትሆን የብፅዓት ልጅ እንደመሆኗ መጠን ለቤተ እግዚአብሔር ተሠጥታ በቤተ መቅደስ አሥራሁለት ዓመት በቅዱሳን መላእክት ተጠብቃ ከኖረች በኋላ በአሥራ አምስት ዓመቷ ማለት አምስት ሺህ አምስት መቶ ዘመን ሲፈጸም ለአዳም የሠጠውን ተስፋ ለመፈጸም በብሥራተ መልአክ በፈቃዱ ከእሷ ተፀነሰ ፤ ተወለደ ። ስለዚህ ድኅነተ ዓለም ተፈጽሟል ። እዚህ ላይ ልንገነዘበው የሚገባ ነገር ቢኖር ፤ ኢያቄምና ሐና በማርጀታቸውና በማፍጀታቸው ተስፋ ሣይቆርጡ ወደ እግዚአብሔር በመለመናቸው ለዚህ ጸጋና ክብር በቅተዋል ። እኛም ያለማመንታትና ያለ ጥርጥር እግዚአብሔርን ብንለምነው ሐሣባችንን እንደሚፈጽምልን ፤ ቸርነቱንም እንደሚለግሠን የታመነ ነው ።

መምህር ኪዳነ ማርያም አየለ



# የሐውልት ምረቃ

ምረቃ ከጥንት ጀምሮ ብሉይ ኪዳንም ከመጻፉ አስቀድሞ ሲሠራበትና መንፈሳዊ በረከት ሲተላለፍበት እንደ ነበረ በመጽሐፍ ቅዱስ ሰፋ ያለ ምዕራፍ ይዞ የሚገኝ ነው ።

እሺ በጀ እያሉ በመላላክ ሺማግሌዎችን ሲያገለግሉና በቅን ልቡና ታኔኘዎች ሁነው ሲገኙ በጎ ታዛዥነታቸውን በመመልከት ይባርኳቸዋል ። እንደዚሁም ሀብትን ፣ በረከትንና ጤንነትንም እንዲያገኙ ይመርቋቸዋል በምረቃውም መሠረት መንፈሳዊ በረከትን ያገኛሉ በሰዎችም ሁሉ ተወዳጅነትን ያተርፋሉ ።

በሌላም በኩል በልዩ ልዩ ነገር አደጋ ደርሶባቸው ዓይናቸው የፈረጠ እጅና እግራቸው የተቆረጠ በጠቅላላ በችግር በረሀብና በእርዛት የሚኖሩ ሰዎች በልተው ሲጠግቡ ለብሰው ሲሞቃቸው ያበላቸውንና ያለበሳቸውን ሰው እግዚአብሔር ሀብቱን እንዲተካለት ይመርቃል ታድያ የዚህ ዓይነት ምረቃ ከዚህ በፊት የነበረ ፣ ዛሬም ያለና የተለመደ መሆኑን የማያውቅ አይገኝም ።

የሚያስገርመውና የሚያስደንቀው ግን የመቃብር ሐውልቱ ወይም የድንጋዩ መመረቅ ነው ሰው በሚሞትበት ጊዜ ሟቹ ሰው ሊደረግለት የሚገባውን ሥርዓተ ጸሎት አድርሶ ከመቅበር በስተቀር ስለሞተው ሰው የራ ?ን ጠጉር መንጩት ፊትን መቧጨር ?ረትንም መድቃትና እነዚህንም የመሳሰሉትን ሕገወጥ ተግባሮች በመመልከት ኦርቶዶክሳዊት ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን በየጊዜው ከማስተማር ከመምከርና ከመገሠጽ ከዚህም በላይ እነዚህ ነገሮች እንዳይፈጸሙ ውሳኔዎን ከማስተላለፍ የተቆጠበችበት ጊዜ እንደ ሌለ በቤተ ክርስቲያን እየታተሙ ለምእመናን የሚደርሱ ጋዜጦችና መጽሔቶች ምስክሮች ናቸው ። ነገር ግን ሕዝቡ ፀተለይ ሴቶች ሰው በሞተ ቁጥር በየመቃብሩ ደረታቸውን ሲደቁ ፊታቸውን ሲቧጭሩ ከመታየታቸውም ሌላ በመካከላቸው አልቃሽ አቁመው ሲያስለቅሱ ማየት ራሱ ያሳፍራል

ይህም አንሶ ባሁኑ ጊዜ ከዚህ በፊት በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ያልታወቀ ከኢትዮጵያም ባሕል የሌለ ይህ የመቃብር ሐውልት ምረቃ እንግዳ ሁኖ ወደ አገራችን መግባቱ የሚያሳዝን ነው ።

በመሠረቱ ሐውልት የሚሠራው ላሉት ሰዎችና ቤተ ዘመድ ማስታወሻ ይሆናል ከማለት በስተቀር ሌላ ረብና ጥቅም እንደ ሌለው ለሟቹ አንድም ነገር እንደማይሠራለት የታወቀ ነው ስለ መቃብር ሐውልት መቋቋምና አሠራር ከዚህ ቀደም ሲል በመጽሔቶችና በጋዜጦች የተተቸ መሆኑን ሳናስታውስ አናልፍም ።

እርግጥ በሲምንቶ ፣ በዕብነ በረድና በልዩ ልዩ የድንጋይ ጥርብ የመቃብር ሐውልቶች ሲሠሩ መቆየታቸውና ዛሬም ሲሠሩ እናያለን ፣ ይሁን እንጂ ብዙ ሺህ ብር ወጭ ተደርጎላቸውና ብዙ የሰው ጉልበት ተሠውቶላቸው ሲሆን በሚገባ ስለማይጠበቁና የሚቆጣጠራቸው ባለ መኖሩ አምረውና አጊጠው ከተሠሩ በኋላ ወድቀውና ተሠባብረው ከጥቅም ውጭ ሁነው ስናያቸው በጣም እናዝናለን ። ይህ ነው እጅግ የሚያሳዝነው ደግሞ ለዚህ መድኃኒት ሳይፈለግለት በመጽሐፍ ቅዱስ ያልተነገረና በቤተ ክርስቲያን ታሪክ የሌለው ከዚህም በፊት ያልነበረ ባህል እንደ ወተት ዝምብ በመካከል ጥልቅ ብሎ የገባው ይህ የመቃብር ሐውልት ምረቃ አሳፋሪ ነው ።

የመቃብር ሐውልቱን መጎናጸፍያ አልብሰውና መቃብሩን ከበው ሥርዓተ ቅዳሴን ማድረሱ ጥቅሙ ምንድን ነው በሐውልቱ ላይ በረከትን ለማሳደር ይሆን ? እዎ የሽማግሌዎች ምረቃና ጸሎተ ፍትሐት የሟቹን ነፍስ እንደሚያስምር እናውቃለን እናምናለንም ። ነገር ግን ድንጋዩንና የመቃብር ሐውልቱን መመረቅ ድንጋዩ እንዲለመልም ነው? ወይስ ሐውልቱ እንዲያድግ ይሆን ?

በእውነቱ ክርስቲያኖች መቃብሩን ከበው ሐውልቱንም አቁመው ካህናትም መጎናጸፊያውን በማልበስ የሚያደርጉት ምረቃ ራስን በራስ እንደማታለል ያስቆጥራል።በራስ መቀለድ በነፍስ መዘበት ተገቢ አይደለም ። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም መዘበት ተገቢ አለመሆኑን ሲያስገነዝብ “እትሳቱ እግዚአብሔር አይዘበትበትምና ገላ.፮.፯ ።

አሁንም ቢሆን አንድ ሰው ከዚህ ዓለም በሞት ከተለየና ከተቀበረ በኋላ እንደገና በትኩስ ሬሳ መልክ ማልቀስና ማዘን ከምን ቀይ ነው ? የዚህን ዓይነት ልቅሶ የቤተ ክርስቲያን ሊቅ ያዕቆብ ። ሥሩግ ሲነቅፍና ተገቢ አለመሆኑን ሲያመለክት“ያን ጊዜ ሐዘን ይደረጋል ። ሐዘኑ ግን የማይጠቅም ሐዘን ነው ፤ያን ጊዜ ጩኸት ይሆናል ግን የማይረባ ጩኸት ነው ” ሲል ከተናገረው ዓረፍተ ነገር ያልተለየ ነው ያዕ ቅዳሴ ቁጥር ፵፤ የሰው ልጅ ለበጎ ነገር ቢቀና ፡ ለምግባረ ሠናይ ቢተጋ መልካም ነበር ግን ዛሬ ተይዞ ያለ እነ እገሌ የመቃብር ሐውልትን ከሠሩና ዘመዶቻቸውን የመቃብር ሐውልት አሠርተው ስም ሲያስጠሩ እኔስ እንዲህ አድርጌ የሞቱ ዘመዶቼን ባስጠራ ማን ይከለከለኛል ከማን እንሽ ነው የሚል ዘመቻ ነው ተይዞ ያለ ዓላማው ግን እውነቱን የሳተ ነው ።

በእውነቱ አባት እናታቸው የሞቱባቸውን ሕፃናት አፍ ዘግቶ የመቃብር ሐውልትን እየሠሩ የሚያስመርቁ በጥቂቱ የሚገሙቱ አይደሉም የዚህ ጥቅምና ለሟቹ የሚሰጠው አገልግሎት ግን ከምን ላይ እንደ ሆነ መልስ የሚሰጥ አንድም ሰው አይገኝም ።

እኛ የምንለው ግን ፭ኛ! ለመቃብር ሐውልቱ የሚወጣው ገንዘብ ያሉት ቤተ ሰቦችና ሕፃናት ቢረዱበትና በ

ወደ ገጽ ፳፭ የዞረ



www.ethiopianorthodox.org

# የግብርና በረከት

በግብርና ነክ ሥራ ላይ የተሠማሩ ሁሉ በሥራቸው ውጤት ተደስተው ሌላውንም ለማስደሰት እንዲችሉ የግብርና ሚኒስቴር በባለሙያዎች የሚፈለገውን እርዳታ እያሟላላቸው ነው ።

በግብርና ሚኒስቴር የማስታወቂያና የሕዝብ ግንኙነት አገልግሎት በወር አንድ ጊዜ እየተዘጋጀ የሚወጣው ዜና ግብርና መጽሔት ስለዚሁ ሁኔታ በየመልኩና በየደረጃው እያዘጋጀ ለየሚመለከተው ይልካል ። እኛም የጽሑፉን ጠቃሚነት በመመዘን በመጽሔታችን እያሠፈርን ለአንባብያን ስናቀርብ ብዙ ጊዜ አሳልፈናል ።

በዛሬው እትማችን በዜና ግብርና መጽሔት ቁጥር ፫ ሚያዝያ ር ፲፱፻፸፮ ዓ.ም ዝግጅት ገጽ ፲፯ ላይ ባለው ያው ይናገር ከሚለው አምድ የተገኘውን አቅርብናል ።




በመጀመሪያ ከዝግጅቱ ክፍል የተሰጠው መግለጫ እነሆ ፡ በሀገራችን የማሣና የጐተራ ተባዮች በግብርና ውጤታችን ላይ የሚያደርሱት ጥፋት ከፍተኛና አሳሳቢ መሆኑ አጠያያቂ ባይሆንም በሀገራችን በተባዮች አማካይነት በምርት ላይ የሚደርሰውን የጥፋት መጠን ለማወቅ ፴% የሚሆን በመስክ ተባዮች ፲% የሚደርሰው ደግሞ በጐተራና መጋዘን ተባዮች በየዓመቱ እንደሚባክን በተባበሩት መንግሥታት የምግብና የርሻ ድርጅት እንዲሁም ከአንዳንድ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች የተገኙ መረጃዎች ያስረዳሉ ።

ይህንን ከፍተኛ የሰብል ምርት ጥፋት ለመቋቋም የተለያዩ ርምጃዎች የተወሰዱና በመወሰድም ላይ ያሉ ሲሆን ከነዚህ ውስጥ አንዱ በምርምር መልክ የሚካሔደው ሥራ ነው በዚህ ረገድ በግብርና ሚኒስቴር ሥር የሚገኘው የሾላ የአዝርእት ጥበቃ ላበራቷር ዋና ዓላማው በምርምርና ጥናት ተቋሞች የተገኙትን ሣይንሳዊ የተባይ መከላከያ ዕውቀትና ቴክኖሎጂዎችን ለገበሬው በልማት ሠራተኞች አማካይነት ምክር በመስጠት በምርት ላይ ይደርሳል ተብሎ የሚገመተውን ጥፋት አስቀድሞ በማስወገድና ተገቢውን ርምጃ በመውሰድ ምርት እንዲያድግ ምርት ሲያድግ በምርቱ የሚጠቀመውን ክፍል ከማስደሰቱም ጋር በአጠቃላይ የምርት ዕድገት ዕገዛ ያደርጋሉ ሲል የዝግጅቱ ክፍል ያለውን አሳብ በማስቀደም ባለሙያው ጠቃሚ ትምህርት እንዲሰጥበት ለባለሙያው አቅርቦታል ።

ባለሙያው ምን አለ ? የባለሙያውን ከሣይንሳዊ ጥናት የተገኘውን ማብራሪያ እንመልከት ልዩ ልዩ ተባዮችን ለማጥፋት የተለያዩ መድኃኒቶች ተገኝተዋል /ተሠርተዋል/ ባለሙያው ስለሾላ የአዝርዕት ጥበቃ ላበራቶር ዓላማዎችና ተግባራት ሲያብራሩ የሾላ የአርዝዕት ጥበቃ ላብራቶር ዋና ዓላማው በምርምር ተቋሞች የተገኙትን ሣይንሳዊ የተባይ መከላከያ ቴክኖሎጂዎች ለገበሬው በማሠራጨት በምርት ላይ ይደርሳል ተብሎ የሚገመተውን ጥፋት በማስወገድ ምርት እንዲያድግ ማድረግ ነው ይልና ዓላማውን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያከናውናቸውን ዝርዝር ተግባሮች ሲያብራራ በጥናትና በምርምር የተገኙትን ፍቱን የተባይ መከላከያ ዘዴዎች በሠርቶ ማሳያዎች ፡ በገበሬ ተወካዮች ሥልጠናና በሌሎችም ዘዴዎች በመጠቀም ለገበሬው እንዲደርሱ ያደርጋል ።

በክፍላተ ሀገር የተመደቡት የአዝርዕት ባለሙያዎች ለአርሶ አደሩ አስተማማኝ የተባይ መከላከያ አገልግሎት ለመስጠት እንዲችሉ የሙያ ማሻሻያ ትምህርት በየጊዜው ይሰጣል ።

አዝርእት ጥበቃ አዲስ ተክኖሎጂ ስለሆነ ሙያውን በስፋት ለማሠራጨት የሚያስችሉ ጥራት ያላቸው መጽሔቶችን ፡ ፖስተሮችን ፡ መመሪያዎችንና አስቸጋሪ ተባዮችን ናሙና በማዘጋጀት ለመስክ ሠራተኞች ያከፋፍላል

በየአካባቢው ጥፋት የሚያደርሱትን የተባይ ዓይነቶችን መጠን ለማጥናትና የሚጠፋውን የሰብል መጠን ለማወቅ አሰሳ ያካሒዳል ።

ከጥቅም ላይ ሳይውሉ ለረጅም ጊዜ በመጋዘን የቆዩትንና ዓይነታቸው ያልታወቁትን ፀረ ተባዮች መርምሮ ጥቅም ላይ እንዲውሉ ያደርጋል ፡

የተምች ወረርሽኝ ለመተንበይ የሚያስችሉ የመብራትና የፎርምን ወጥመዶችን በእስትራቴጅክ አካባቢዎች በማቋቋም መረጃዎችን ይሰበስባል ፡

የተባይ መከላከያን በሚመለከት ለመንግሥታዊና በሕዝባዊ ድርጅቶች እንዲሁም ለግለሰቦች ምክር ይሰጣል ። ባለሙያው ይህን ካብራራ በኋላ በላቭራቶሪው ስር የሚገኙትን የሥራ ዘርፎች በሚከተለው ዓይነት በዝርዝ አስቀምጦ ለተጠቃሚው አሳይቶአል ። ይኸውም "ላቭራቶሪው በእርሻ ልማት መምሪያ በአዝርዕት ጥብቃ ቡድን ሥር የሚገኝ ሲሆን በውስጡ ያሉ የሥራ ዘርፎች

፩. ኢንቲሞሎጂ ነፍሳት ተባይ
፪. የእጸዋት በሽታ
፫. የአረም መከላከል
፬. የጐተራ ተባይ መከላከል
፭. የፀረ ተባይ ኪሚስትሪ
፮. የዓይጥ መከላከያ ናቸው ።

እንግዲህ ስለዚህ የላቭራቶር አሠራር ባለሙያው በሰፊው አብራርቶአል ቀሪውን ክፍል በሚቀጥለው እትማችን የምናቀርብ ሲሆን በልማት ሥራ የተሠማሩ የቤተ ክርስቲያን የልማት ክፍል ባላቸው ችግር መፍትሔውን ከዚህ የዜና ግብርና ዝግጅት ክፍል ሊረዱ የሚችሉ መናናቸውን በዚህ አጋጣሚ እንጠቁማለን ።

ፍሥሐ ባንቴ



www.ethiopianorthodox.org

# ሕፃኑ ከእናቱ ጋር

የተፈጥሮ ሕግጋት እንደ ሚአስረዱን ምድር ያለዘር አብቅላ ፍሬ ለመስጠት እንደማትችል ሁሉ ልጅም ያለእናትና ያላባት ለማገኘት አይቻልም ።

ዘርንም ከእንሳን ዘንድ ስለ አበቃቀሉ በአጭሩ መጥቀሱ አስፈላጊ ነው ። በመልካም መሬት ላይ የወደቀ ዘር በጥሩ ሁኔታ በቅሎ አድጐ ጠቃሚ ፍሬ ይሰጣል ካልሆነ መሬት የወደቀ ዘር ግን ለጊዜው ቢበቅልም ከጥቂት ቀን በኋላ ጠ ውልጐ ደርቆ እንዳልነበረ እንደ ሚሆን በሁላችን ዘንድ አጠያያቂ ሊሆንብን አይችልም ።

በዚህ አንፃር ከአልሆነ ቤተሰብ የሚወለድ ልጅም አስተዳደጉ በመልካም ስነ ባህርይ ያልተመሠረተ በመሆኑ በሕፃንነቱ ዘመን የሚከሰተው ጠባዩ የሚአስደስት ሳይሆን የሚአሳዝንና የሚያሳፍር ታማኝነት የሌለው ለሰውም ሆነ ለእግዚአብሔር የማይመች ይሆናል ። አባቶቻችንም ሲመርቁ ወልዶ መካን ከመሆን ያድን የሚሉት ከዚህ የተነሳ ነው ።

በተለይም ከመልካም ቤተሰብ የሚወለድ ልጅ ደግሞ በሥነ ሥርዓት ታንጾ በሃይማኖት ጸንቶ የአባቱንና የእናቱን ትእዛዝ እየተቀበለና እየፈጸመ ስለሚያድግ የሚገጥመው እድል ክብርና ፀጋ እውቀትና ጥበብ ሆኖ ፣ እግዚአብሔርን ፈሪ ሀገሩን አክባሪ ፍጹም ታማኝ ዜጋ ይሆናል ።

ይህን ሁሉ ለመዘርዘር የሞከርነው ከላይ በርእሳችን የገለጽናቸውን የሕፃኑን ቅዱስ ቁርቆስንና የእናቱን ቅድስት ኢያሉጣን ታሪክ በመጠኑ ለመግለጽ ነው ።

እንባብያን የሁለቱን ታሪክ ከመተንተናችን በፊት ለታሪካቸው በር ወይም መግቢያ ይሆን ዘንድ በትንቢተ ኢሳይያስ ከምዕራፍ ፳፱ ቁጥር ፩-፰ ያለውን ቃል መጥቀሱ ለሁላችንም ትምህርት ሊሆነን ይችላል ።

እኔ እግዚአብሔር በጽድቅ ጠርቼሃለሁ እጅህንም እይዛለሁ እጠብቅሃለሁ የእወሩን ዓይን ትከፈት ዘንድ የተዘጋውንም ከግዞት ቤት በጨለማ የተቀመ



ጡትንም ከወህኒ ቤት ታወጣ ዘንድ ለሕዝብ ቃል ኪዳን ለአሕዛብ ብርሃን አድርጌሃለሁ ይላል ።

ከላይ በተገለጸው ቃል መሠረት እግዚአብሔር ቅዱስ ቁርቆስንና ቅድስት እየሉጣን ልቡ ናቸውን በእምነት አዕምሮአቸውን በእውቀት ስለጐለመሰው እስክንድሮስ የተባለ ከሐዲ እግዚአብሔርን ከማምለክ ተመልሰው ጣዖትን እንዲአመልኩ ቢጠይቃቸው እኛስ የምናመልከው ያለ የነበረውን ለወደፊትም ፀንቶ የሚኖረውን እግዚአብሔር አምላካችንን እናመልካለን እንጂ ጣዖት አናመልክም ቢሉት ተናዶ የተለያዩ ፀዋትወ መከራ እንዲፈጸምባቸው አድርጓል ።

ቢሆንም ሕፃኑ ቅዱስ ቁርቆስና እናቱ በጥኑ ስነ ምግባርና በሃይማኖት የፀኑ በመሆናቸው ሊሸከሙት የማይችሉትን አሰቃቂ መከራ ወርቅ በእሳት እንደ ሚፈተን ቢፈትናቸውም ሁሉን ነገር የሚአስችል ሕያው እግዚአብሔር በእኩቱት እንዲቀበሉት አድርጓቸዋል።

በማቴዎስ ወንጌልም ምዕራፍ ፲ ከቁጥር ፳፰ ላይ ሥጋን የሚገድሉትን ነፍስን ግን መግደል የማይችሉትን አትፍሩ ይልቅስ ነፍስንም ሥጋንም በገሀነም ሊአጠፉ የሚቻለውን ፍሩ ስለሚል ቅዱስ ቁርቆስና እናቱም ሣያመንቱ የወንጌሉን ቃል በተግባር አውለውታል።

በሕፃኑና በእናቱ እየሉጣ ላይ የደረሰባቸው ሥቃይ ሰው በድለው የሰው ሀብት ቀምተው ወይም ልዩ ወንጀል ፈጽመው ሳይሆን እግዚአብሔርን እንጂ ጣዖትን አናመልክም ብለው በሃይማኖታቸው በመጽናታቸው ብቻ ነው ።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም በሃይማኖት መጽናትና መበርታት እንደ ሚገባ ለቆረንቶስ ሰዎች ሲገልጽ ጽድቅ ከአመጽ ጋር ምን ተካፋይነት አለውና ? ብርሃን ከጨለማ ምን መስማማት አለው? የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ከጣዖት ጋር ምን መጋጠም አለው እኛ የእግዚአብሔር ቤተ ነንና ። እንዲሁም እግዚአብሔር ተናገረ እንዲህ ሲል በእነርሱ እኖራለሁ በመካከላቸውም እሆናለሁ እነርሱም ሕዝቢ ይሆናሉ ። በማለት አስቀምጦታል ። ሁለተኛ ቆረንቶስ ም፮. ቁ. ፲፬-፲፮ ።

ቅዱስ ቁርቆስና ቅድስት እየሉጣም ከላይ በተገለጸው መሠረት ወደ እሳት ቢጣሉም በእግዚአብሔር አጋዥነት በቅዱስ ገብርኤል ተራዳኢነት የፈላውውን በመቀዝቀዝ ሰውነታቸውን ሊጐዳው አልቻለም ።

ከዚህ ላይ ለአንባብያን የምንገልጸው ነገር ቢኖር በፈጣሪ አምላኩት የሚጸኑትን ሁሉ ከማንኛውም ችግር የሚጠብቃቸው መሆኑን መረዳቱ ጠቃሚ ነው።

ሕፃኑ ቁርቆስም ገና በእናቱ ማሕፀን ሳለ መንፈስ ቅዱስ ስለአደበረት በ፫ ዓመቱ ይህንን የመሰለ ተጋድሎ ሊፈፀም ችሏል ።

ቅዱስ ቁርቆስ እንደ ቅዱስ ዮሐንስ በኅፃንነቱ መንፈስ ቅዱስ ስለ ሞላበት እናቱ እያሉ የፍርሃት መንፈስ ቢአድርባት እናቴ ሆይ አትፍሪ አይዞሽ በርቺ በማለት አጽንቷታል።እንዲሁም ሕሙማንን ፈውሷል።ልዩ ልዩ ታምራቶችንም አሳይቷል ። ያደረገውን ታምራት ያዩና የተመለከቱ ሁሉ ካለ ማመን ወደ ማመን ተመልሰዋል ።

በአጠቃላይ ቅዱስ ቁርቆስና እናቱ ቅድስት እየሉጣ ፈተናን ሁሉ በትዕግሥት በመቀበላቸው ከፈጣሪያቸው የጽድቅ አክሊልን ተቀናጅተዋል ። ሰማያዊ ክብርንና ፀጋን አግኝተዋል።

መሪጌታ ተሰማ ገ/ሚካኤል

# የሐውልት ምርቃት

ከገጽ ፲፯ የዞረ

ማሩበት ።

፬ኛ/ በቤታቸው የሚቀመስ ቁራሽ የሚለበስ ብጣሽ አጥተው በረሀብና በእርዛት ለሚኖሩ ሰዎች ቢሰጥና ችግረኞች ቢረዱበት ለሟቹ የበለጠ ተስፋ በሆነው ነበር ። በመጨረሻ ግን ልናሳስበውና ልናስገነዝበው የምንፈልገው ቢኖር ካህናት ለሟቹ ሰው የሚጠቅመውን ነገር መምከርና ማስተማር ሲገባቸው የመቃብር ሐውልትን ማስመረቅ ተገቢ ነው ፤ ድግስንም ደግሶ ማብላትና ማጠጣት አስፈላጊ ነው ፣ ብለው የንሥሐ ልጆቻቸውን ማስተማር ቢተውና በመቃብር ሐውልቱ ምረቃም ባይገኙ መልካም ነው እንላለን ።

ከነፈ ርግብ ማርቆስ





www.ethiopianorthodox.org

# ማንን ላግባ

ካለፈው የቀጠለ ክፍል ፺

ብሔሮች በሃይማኖትና በባህል በሥርዓት ይለያያሉ ሁለንተናው መልክ ያለው የጋብቻ ስርዓትም እንዲሁ የተለያየ መልክና ቅርፅ አለው ለምሳሌ አየርላንድን ስንመለከት አንዲት ሴት አግብታ ከፈታች (ባሏ ከሞተባት) ሁለተኛ እንድታገባ አይፈቀድላትም የዚህ አይነቱ የጋብቻ ሥርአት ፍትሐ ብሔርና የመተዳደሪያ ደንቦች ይቀበሉት እንደሆን እንጂ በመጽሐፍ ቅዱስ የጋብቻ ሕግ ጨርሶ ተቀባይነት የለውም ።

ሰማንያ ከጋብቻ አይነቶች አንዱ ነው በሐገራችን ባህል የተለያዩ የአስተሳሰብና ትርጉም አስከትሎ አጠያያቂ ሆኖአል ። የማህበረሰብ ሳይንስ ጥናት ያካሔዱ ሙሁራንም የ፹ኒያንመነሻና መድረሻ ለማወቅ ሙከራ ያካሔዱ ይሁን እንጂ በጥናት የተደገፈ ጭብጥ ማስረጃ ማቅረብ አልቻሉም አብዛኛዎቹ ፹ በሃገር ልማድና ወግ የመጣ ነው እንጂ በነገሥታትና በመሳፍንት የግዛት ዘመን የተከሰተ አይደለም ብለው ያምናሉ ። ለሃሳባቸው መንደርደሪያ ያደረጉትም የታሪክ መዝገብ ስንመለከትአፄ እከሌ (መስፍን እገሌ) በ፹ ተጋቡ የሚል ታሪክ መረጃ ስላላገኘን ነው ይላሉ ። አንዳንዶቹ ደግሞ በራሳቸው የመላምት እስተሳሰብ ያልተጨበጠውን የ፹ የታሪክ አመጣጥ ያወጋሉ ። ለዚህም የሚጠቀሙበት ተረት በ፲፰ተኛ ክፍለ ዘመን በጐንደር ክፍለ ሀገር ቋራ ተብሎ የሚጠራው ሥፍራ አንድ ሰውየ አንድን ልጃገረድ ለማግባት ፈለገ ለእጅ መንሻ የሚሆን ፹ ብር ሰጣት ከ፪ ዓመት በኋላ ሲፋቱ የሰጣትን ፹ ብር ለሁለት ተከፋፍለው ተለያዩ ብለው ይተርታሉ ።

ይህም ለመመሪያና ለጥናት ይጋብዝ እንደሆን ተብሎ ከአንዳንድ ጋብቻ ማህደር ይገኛል ። ነገር ግን ይህ ጽሑፍ ኃላ ያሉ ስህተቶችን ይዞ እናገኘዋለን ።፩ኛ የሰማኒያ ውል የሚፈፀመው በሰፈር ሽማግሌዎች ዳኝነት ሲሆን ፹ ማፍረስ (ማስወረድ) ማለት የጋብቻውን የውል ሰነድ ቀዶ ማለያየት ማለት ነው ። አከራካሪ ባለመሆኑ ላነሳው ያልፈለግሁት ጥያቄ ቢኖር የገንዘብና የኀብረት መከፋፈል በየትኛውም ህግ ተጋቢዎች ሲለያዩ ክፍፍሉ የማይቀር በመሆኑ ነው የሰማኒያው ውል ዋናው ቁም ነገሩ ግን እፍራሹን ወገን ሕግ ፊት አቅርቦ ማስቀጣት ወይም ማስማማት እንዲፈጠር ለማድረግ ነው ። በኢትዮጵያ ፍትሐብሔር ሕግ ፹ ሆነ ሌሎችን የጋብቻ አይነቶች ሊያፈርሱ የሚችሉ ከ2 ወገን አንዱ የአእምሮ መታወክ ያለበት እንደሆን ፡ ያለፈቃድ ከ፪ ዓመት በላይ የቆየ እንደሆን ፡ ሰባት ትውልድ የማይሞላ ዝምድና ሐረግ በተጋቢዎች መካከል የኖረ እንደሆን ፡ የግንኙነት ተግባር ማከናወኛ አካል በህመም ምክንያት የተሰናከለ እንደሆን ፡ በእነዚህ ምክንያቶች ብቻ ሰማንያም ሆኑ ሌሎች የጋብቻ አይነቶች ሊፈርሱ እንደሚችሉ ይገልፃል ስለዚህም ሰማንያ የተጋቢዎችን ጥፋት ለመደንገግ የተፈጠረ የጋብቻ መንገድ ነው ብንል እንሳሳትም ።



ጽሑፉን በተከታታይ ያቀረበልን ቀለመ ወርቅ መአሾ ይህ ነው

፪ኛ/ በሰማንያ የሚጋቡ ባልና ሚስቶች በተለያየ አጋጣሚ የተገናኙ ፊት የነበሩ ፡ በግንኙነት የተጣጣሙ በመሆናቸው ፍቅራቸው አልቆ ጠብና ጭቅጭቅ ሲያነሱ የኑሮ ኩንትራታቸው የሚያከትምበት ልል የሰነድ ውል ነው ። ይኸውም ሁለቱ እንደወደዱ የሚገነቡትና ፡ እንደ ወደዱ የሚያፈርሱት በመሆኑ ነው ይልቁኑም ስለ ሰማንያ የሃይማኖት ሊቃውንት የሚሰጡት አስተያየት አለ ።

ይኸውም የ፹ ባልና ሚስት ማለት ሁለቱ ተጋቢዎች እስከ ህይወታቸው መጨረሻ ድረስ ተስማምተው ተዋደው ኑሮአቸውን የሚያካሄዱበት ገደብ ነው ግን ፹ ማለት እንደ ፲ ፶ ፷ ፸ ቁጥር ሳይሆን ምክንያት ያለው ቁጥር ነው ይኸውም ሰው ሲሠራና ሲያሠራ ኑሮ ሕይወቱን በጤንነት ሲመራ ቆይቶ ህይወቱ የሚፈፀመው የሚያልቀው በ፹ ዓመቱ ነው ይኸውም በአማካይ ደረጃ ነው ።

መዝሙረኛው ዳዊት በመዝሙር ፹፱/፺ በቁጥር ፲ "የዘመናቻችንም ዕድሜ ሰባ ዓመት ፡ ቢበዛም ሰማኒያ ዓመት ነው ከዚያ ቢበዛ ግን ድካምና መከራ ነው" ብሎአል ስለዚህ ባልና ሚስት በተድላ በደስታ የሚኖሩት እስከ ሰማኒያ ዓመት መሆን ይገባል በማለት ሰማኒያ የተባለበት በዚህ ምክንያት ነው።ይኸውም ከሞት በስተቀር ማንኛውም ነገር በኩርፊያ ፡ በጥላቻ መለያየት እንደማይገባቸው የማስተማመኛ ቃል ኪዳን ነው ብለዋል ።

ጋብቻ ዛሬ ተገንብቶ ነገ የሚናድ እንደ ህፃናት ጨዋታ ሣይሆን ለደስታና፡ ለሃዘን ፡ ለተድላና ለመከራ ባጠቃላይ በሰው ኑሮ ገጠመኝ ለሚፈራረቁት የማህበራዊ ኑሮ ጠባዮች መድህንና መቆሚያ በመሆኑ እንደ ሊቃውንቱ አባባልና እንደ እግዚአብሔር ቃል ተጋቢዎች በተክሊልና በቁርባን ተወስነው አንድ ጊዜ ከተካበ የማይናድ ስሙር ክርስቲያናዊ ጋብቻ እንዲመሠርቱ የሚገፋፋና የሚያበረታታ ነጥብ ነው ።

ሰው በሕግ ተጋብቶ በመንግሥት የታወቀና በፍትሐብሔር የተደገፈ የጋብቻ ሠርተፍኬት (የማረጋገጫ ወረቀት) አግኝቶ ከፍርድ ሳብ ጐተቱ ጽኖ በኑሮው ሁሉ የታመነና የተጨበጠ የጋብቻ እንዋዋር መፍጠር ስለሚገባው ሙግት የሚቀርብበት ጉዳይ አይሆንም ለዚህም ብሔሮች እንደየአገሮቻቸው ደንብ መንግሥታዊ ስልጣንና አደራ የተሰጠው ክፍል አቋቁመውለታል ለምሳሌ ሃገራችን የዚሁ ክፍል ሃላፊነትና ስልጣን ተረክቦ የጋብቻን ውል የሚያፈጣጥመው መዘጋጃ ቤት (የከነማ ማዕከል) ነው ። የመዘጋጃ ቤቱ የጋብቻን ውል ፍጥምጥም ብሔራዊና አለም አቀፋዊነት ያለው የምስክር ወረቀት ስለሚሰጥ እንደሰማንያው ልማዳዊ የውል ደንብ አከራካሪና አጨቃጫቂ አይሆንም ጥብቅ እንጂ ልልም አይደለም ። ሁለቱን እያወዳደርን ብንመለከት በተለይ የሰዎች አዕምሮ በዕውቀት ዳብሮ ተንኰልና ሸር በበዛበት በ፳ኛው ክፍለ ዘመን በሽማግሌዎች ይፈጸም የነበረው የሰማንያ የውል ወረቀት ጋብቻውን ለማፍረስ ያሰበ ወገን በቀላሉ ሊያጠፋውና ሊያበላሸው ስለሚችል ሁለተ^ውን ወገን የሚጐዳና በፍርድ ማስረጃ የሚያሳጣ ነው ።

ጠው በመሆኑ ግፍ ለመፈጸም ያሰበው የ

የመዘጋጃ ቤቱ የጋብቻ ውል ግን መንግሥት ያወቀውና ህጋዊ ሰውነት የሰጠው በመሆኑ ግፍ ለመፈጸም ያሰበው የጋብቻ ተቀዋሚ ሊያገኘው ስለማይችል በደልና ግፍ የተፈጸመበትን አግቢ ማስረጃ እንዲያገኝ ከመርዳቱም በላይ የተስተካከለ ፍትህ፡ና የሕግ መብት ያለው መሆኑን ያረጋግጥለታል ። በተጨማሪም ለአንድ ሃገር የህዝብ ቁጥር በትክክል መታወቅ አስተዋፅኦ ያለው ነው ። በጣሊያን ሃገር ሮማ ከተማ ከ፶ አመት በፊት የነበሩ ወ/ሮ ማርያ አንቶንዮ ሰባት ባሎቻቸውን በህግ አግብተው በ፴ ቀናት ውስጥ በህግ ፈትተዋል ። የወ/ሮ ማርያን ታሪክ ማወቅ የቻልነው ሕግ ያወቀውን ነገር ለመፃህፍት አታሚዎችና ለዜና አቅራቢዎች በአሳዛኝነቱምሆነ በአስደሳችነቱ እንዲገለፅ ተብሎ ስለሚሰጥ ያለፈውን ስህተት ሌሎች እንዳይደግሙት ግን የመንደርና የሰፈር ሽማግሌዎች በልማድ የሚሰሩበትና ባህል ብለው የሚሰሩበትና ጐልቶ የሚታይ ታሪካዊ ነጥብ ያለውም በመሆኑም መሻሻል የሚገባው ጥናትና ምርምር የሚያስፈልገው ነገር ነው ።

ከአራት መቶ ዓመት በፊት የነበረ ቻይናዊው ደራሲ ባለቅኔውና ፈላስፋው ፎፍማን "ዘዌይ ኑፍ ክርስቲያኒቲ" (የክርስትና እምነት ትርጉም) በሚለው መጽሐፉ አግቢዎችን ሲመክር ጋብቻችሁ በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት እንዲኖረውና እናንተም ምድራዊ ደስታ እንድታገኙበት በሃገር ሕግና በቤተክርስቲያን ሥርዓት የፀደቀ ይሁን " ብሎአል ። እርግጥ ነው ሁለቱ ደንቦች ህብረተሰቡ ሊቀበላቸው የተገቡ ድንቅ ድንጋጌዎች ናቸው ። ሕዝቡ ግን በይበልጥ የለመደውና የተቀበለው ልማዳዊ ሥርዓት ነው ። የታደሉት ክርስቲያኖች ግን በምድር ያለነው ጊዜያዊ ድንኳን ከሚያምርልን ይልቅ የዘለዓለም መኖሪያችን የሆነውን መንግሥተ ሰማይ የዕድቅ ቦታ ወራሽ ብንሆን ይሻለናል።አበሳና ኩነኔ እንዳይደርስብን የዘላለም ሞት እንዳያገኘን ብለው በአንድ ሚስት ጸንተው ቅዱስ ሥጋውንና ክቡር ደሙን ተቀብለው በጾም በስግደት ተወስነው አምላካቸውን እያመሰገኑና በጸሎት እየለመኑ ይኖራሉ ።

እንደ እኔ አስተያየት የምድሩ ሕግም እንደዚሁ መፈራትና መከበር ይኖርበታል ። ለምን ቢባል ከጭቆጭቅና ከመከራ ለመዳን ፡ ከእስራትና ከገንዘብ ቅጣት ለመራቅ ብቸኛ መንገድ የሆነ ሕግ ነውና እንዲሁም ሕግ አክባሪ ከሆን በህዝብና በመንግሥት የተመሰገነ ትሁትና ግብረገብ በመሆኑ ለትልቅ ኃላፊነት ሊመረጥ የሚችል በመሆኑ ለሕዝባዊ ስርአትና ለትክክለኛ ዳኝነት ኃላፊነት የሚጣልበት ሰው ይሆናል ።


ዴል ካግ ኔጂ የተባለ አሜሪካዊ የማህበራዊ ሳይንስ ጥናት ዶክተርም ሃውቱው ግን ፍሬን ስ ኤንድ ኢንፍሎንስ ፒፕል በተሰኘው መጽሐፉ "ከባለቤቴ ጋር ፍቅር አለኝ ሁል ጊዜ ፈገግታን እሳያታለሁ በዝሙትም አልጠረጥራትም በህግ ያገባኋት ሚስቴ ናትና ጋብቻ ብታፈርስ ህግ ይጠይቃታል የሚል ጨዋታ አንድ ጃፓናዊ አጫወቱኝ ሲል ጽፎአል" ይህም ጨዋታ ቁም ነገር ያለው በመሆኑ እኛም ልናደንቀውና ልንቀበለው የሚገባን ነው ምን ጊዜም ቢሆን በተጋቢዎች መካከል እምነትና መከባበር መተያየት አለበትና ነው ። ያም ሆነ ይህ ጋብቻ የኑሮ መሠረት የህይወት ማዕከል በመሆኑ የማይፈርስና የማይነቃነቅ ቤት ለመመስረት የሁላችን አክብሮትና ፍላጐት መሆን አለበት እላለሁ እንግዲህ ጋብቻችን በሰማኒያ ወይም በልማዳዊ ጋብቻ ሳይሆን በመንግሥት ህግና በቤተ ክርስቲያን ተክሊል የፀደቀ ይሁን በሚቀጥለው ጽሑፍ በሌላ ርዕስ እንገናኝ ።

ቀለመወርቅ መአሾ





www.ethiopianorthodox.org



በምድረ ጅቡቲ በመሠራት ላይ የሚገኘው ምሥራቀ ፀሐይ ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን ይህ ነው ፤



# ኢ.ኦ.ተ.ቤ.ክ

የሰብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልዕኮ መምሪያ ፡

ማሳሰቢያ ለምእመናን በሙሉ ፤

የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ታሪክ ፣ ጸዋትወ ዜማዎችንና ቅዳሴዎችን ፤ መንፈሳዊ ዘመናዊ መዝሙሮችን ፤ ትምህርቶችንና የልማት እንቅስቃሴዎችን ሁሉ እየ ተከታተለ በቴፕ እየቀረጸ ለቤተ ክርስቲያኒቱ ቋሚ ቅርስ ያስቀምጣል ። ይህንኑ ለሚፈልጉ ግለ ሰቦ ችም ሆኑ ድርጅቶች የካሴት ክር ላቀረቡ ያገልግሎት ሁለት ብር ብቻ በማስከፈል ይሰጣል ።

ለዚሁ ጥያቄ ቢኖርዎ ከድርጅቱ በመምጣት ወይም ስልክ በመደወል ለመረዳት ይቻላል ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
የሰብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልዕኮ መምሪያ
የካሴት ሐዋርያ አገልግሎት ፤

የስልክ ቁ. 116616
የመልእክት ሣ. ቁ. 3137
አዲስ አበባ ፤

www.ethiopianorthodox.org